# ከቀበና ማህደር

ከአገር ውጪ የሚኖሩ የቀበና አብሮ አደጎች ዓመታዊ መሰባሰቢያ ቀንን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀ መጽሔት

ቁጥር 2 - ሰኔ 2007 ዓ.ም | ሲልቨር ስፕሪንግ ፣ ሜሪላንድ ፣ አሜሪካ | www.yekebenasefer.com






ቀበና፤ ቀበና፤ ቀበና ፈና

ኤሳ፤ ቢሻን ቀበና

ደራሽ ውሃ ከላይ

ከእንጦጦ ድልድይ ላይ

ከአጎዛው ተሻግሮ ተባለ ቡልቡላ።

በጋም ሆነ ክረምት በጸሀይ ዳመና

ከዚያም ከዚህ መጥተን ዋኝተናል ቀበና

ፍቅር አጠራርቶ ከፈረንሳይ ቤላ

ቀበና ታደምን ከአቧሬ እስከ ሾላ።

ምንም ብንራራቅ ቢለያይ ደብራችን

ከማዶ እስከማዶ አንድ ነው ወንዛችን።

ያ ሰናይ ዘመን የልጅነቴ

ቢሻን ቀበና ነው መሰረቴ።

የማልዘነጋው ቡረቃ ኩሬ

የዋኘሁብሽ ጥንስስ ባህሬ።

የሽሮ ሜዳ ነኝ፤ ወንዜ ቀበና

የፈረንሳይ ነኝ ወንዜ ቀበና

የኣራት ኪሎ ነኝ ወንዜ ቀበና

የቤላ ልጅ ነኝ ወንዜ ቀበና

የጃንሜዳ ልጅ ነኝ፤ ወንዜ ቀበና . . .

በዘመን ኮርቻ ቢገሰግስ ጊዜ

የልጅነት ሳቄን አስታወሰኝ ወንዜ

የደስታችን ጥምቀት የጨቅላነት ቃና

እንዲህ ነው ፍቅራችን ወንዛችን ቀበና።

ከአብሮ አደጎቼ ቡረቃው ያኔ

ዛሬም ላይ አለች መነጽር ካይኔ

የዘላለሜ ትዝታው ቃና

ሁሌም ታሪኬ ወንዜ ቀበና

የጃንሜዳ ነኝ ወንዜ ቀበና

ኮሪያ ሰፈር ነኝ ወንዜ ቀበና . . .

ቢሻን፤ ቢሻን ቀበና

# ከቀበና ማህደር

ከአገር ውጪ የሚኖሩ የቀበና አብሮ አደጎች ዓመታዊ መሰባሰቢያ ቀንን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀ መጽሔት

ቁጥር 2 - ሰኔ 2007 ዓ.ም | ሲልቨር ስፕሪንግ ፣ ሜሪላንድ ፣ አሜሪካ | www.yekebenasefer.com

## ማውጫ

ገፅ 2
የመጽሔቱ አዘጋጆች መልእክት

ገፅ 3
አብሮ አደጎች ምን ይላሉ?

ገፅ 5
የልጆች አምድ

ገፅ 7
እስቲ እናስታውሳቸው

ገፅ 17
ከዚህም ከዚያም

ገፅ 22
የቀበና ትዝታ

ገፅ 33
የፎቶ ዓምድ

አስተያየትዎንና ሌላም መልዕክትዎን በዚህ ይላኩልን
myrootkebena@yekebenasefer.com



ዋና አዘጋጅ

ወርቁ ዳመና

የኤዲቶሪያል ኮሚቴው አባላት

ገዛኸኝ ታደሰ
ግርማ ታደሰ
ሰለሞን ሃድጎ (ጋንፉር)
ሰለሞን አስፋው
ዶ/ር ጌታቸው በላይነህ

## ምስጋና

በአምናው (2014) የአብሮ አደጎች የመሰባሰቢያ ቀን ዝግጅት ላይ ከተገኙና ከዚያም በኋላ የአብሮነት ስሜታቸውን ለመግለጽ ከፈለጉ የቀበና ልጆች ከዚህ የሚከተለው የገንዘብ ስጦታ መሰብሰቡን ከከፍተኛ ምስጋና ጋር ለመግለጽ እንወዳለን።

| | |
|---|---|
| ዮሐንስ ገብረሥላሴ | 100 |
| አሸናፊ ተፈራ | 60 |
| ደረጀ ሃብቴ | 150 |
| ፋኖስ ሃብቴ | 50 |
| አልማዝ ሃድጎ | 200 |
| መሰረት፤ ሒሩት፤ ስምረት ና ሃረገወይን በቀለ | 350 |
| ምስራቅ አለማየሁ | 50 |
| ይትባረክ ጀምበሬ | 50 |
| መላኩ | 100 |
| ዕፀ ገነት ሳህሉ | 100 |
| ቴዎድሮስ | 50 |
| እመቤት ሲሳይ (መኰንን) | 50 |
| አስራት ታደሰ | 50 |
| እናና (ኢትዮጵያ) አለማየሁ | 50 |
| ከተለያዩ ሰዎች በሳጥን የተሰበሰበ | 264 |
| ድምር (በአሜሪካ $) | **1674** |

Kwik Design & Printing
www.kwikdp.com • 619-206-0921 (Assaye)
Printed in U.S.A

# የአዘጋጆች መልዕክት

በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጪ በተለያዩ የዓለም ማዕዘናት ተበታትናችሁ ለምትኖሩ የቀበና አካባቢ አብሮ አደጎቻችንና ቤተሰቦች ሁሉ ሰላምታችን ይድረሳችሁ።

አምና ለመጀመሪያ ጊዜ ታትሞ የተሰራጨውን "ከቀበና ማህደር" ተከታይ ይዘን ስንቀርብ ደስታችን ከፍ ያለ ነው። ዘንድሮ ይሳካልናል የሚል ግምት አልነበረንም። ባለቀ ሰዓት ያለ የሌለ አቅማችንን አሰባስበን ባደረግነው ጥረት እነሆ ቁጥር 2 እውን ሆነ። መጽሄቱ የትስስራችን መገለጫና ማጥበቂያው ነው ብለን እናምናለን። ይሄን እምነት የምትጋሩን እና ትስስሩ ዘላቂ እንዲሆን የምትሹ ከሆነ፣ የቅርብ ትብብራችሁ የማይለየን፣ ማለትም ካደግንበት አካባቢ ጋር የሚያያዙ እውነተኛ ታሪኮችን ወይም ታሪክ ቀመስ ወይም የልብ ወለድ መጣጥፎችን በማቅረብ፣ አስተያየታችሁን በመግለጽና በመጽሄቱ ህትመትና ስርጭት ተሳትፎ የምታደርጉ ከሆነ፣ መጽሄቱ በያመቱም ባይሆን በየሁለት ዓመቱ ተዘጋጅቶ መቅረብ ይችላል።

## ያለፈው አንድ ዓመት ታዲያ እንዴት አለፈ ?

አዎ፤ አንዳንዶቻችን ሀዘን፣ ሌሎቻችን ደግሞ ደስታና ስኬት አስተናግደናል። ደስ ከሚሉትና ሁላችንንም ከሚመለከተው ብንጀምር፤ የሰፈራችን ልጅና አብሮ አደጋችን ዝነኛው ድምጻዊ ፀሐዬ ዮሀንስ "ቀበና" በሚል ርዕስ ያቀረበው በተንቀሳቃሽ ምስል ጭምር የታጀበ ጥዑመ ዜማው ሊጠቀስ የሚገባው ነው። ዘፈኑም ሆነ የምስል ቅንብሩ በትዝታ ጭልጥ አድርጎ እንደወሰዳችሁ መገመት አይከብድም። እናመሰግናለን ፀሐዬ ! እኛ "ቀበና" ብለን ስንነሳ አንተም "ቢሻን ቀበና" ብለህ በውብ ድምጽህ አዜምህልን፤ የቀበናን የህዝብ መዝሙር አበረከትህልን። ዘፈኑን የሰሙ የቀበናና የአካባቢው የአሁን ነዋሪዎች ከሙዚቃው ጋር አብሮ ለመንቀሳቀስ መሞከራቸው፣ የቀድሞዎቹ ደግሞ በትዝታ ባህር ውስጥ መስመጣቸው የማይቀር ነው።

በሌላ በኩል ባለፉት ጥቂት ወራት ውስጥ ሁላችንንም ካሳዘኑት ክስተቶች ደግሞ በደቡብ አፍሪካ ጠባብ አገረኞች፣ በሊቢያ በሃይማኖት ስም የደም ጥመኞች እና በየመን የእርስ በርስ ጦርነት ተፋላሚዎች ሳቢያ በኢትዮጵያውያን



አብሮ አደጎችን የማሰባሰቡን ተግባር የሚያስተባብሩት

ወገኖች ላይ የደረሰው አሰቃቂ ግፍ ነው። በስደተኛ ወገኖቻችን ላይ በደረሰው መከራ በጋራ የሀዘን ድባብ ውስጥ ከርመናል።

በዚህ ሁሉ መካከል ግን ህይወት ይቀጥላል። የኋላውን፣ ያለፈውን ሳንረሳ ወደፊት መጓዛችን የግድ ነው። ለዚህ ነው "ከቀበና ማህደር" ቁጥር 2 ታትሞ መቅረቡ፤ የዘንድሮ የአብሮ አደጎችና ቤተሰቦቻቸው የመሰባሰቢያ ቀንም ጊዜውን ጠብቆ መዘጋጀቱ።

አምና ለመጀመሪያ ጊዜ ታትሞ የወጣው መጽሄታችን በአገር ቤትም ከአገር ውጪም ላሉ አብሮ አደጎቻችንና ዘመዶቻችን በተቻለ መጠን እንዲደርስ ተደርጓል። በጠቅላላው 200 ያህል ኮፒ ኢትዮጵያ ተልኮ በቀበና አካባቢ ሲሰራጭ፤ ሌላ 200 ያህል ኮፒ ደግሞ ከኢትዮጵያ ውጪ በአሜሪካ፣ ካናዳ፣ እንግሊዝ፣ ጀርመንና አውስትራሊያ ላሉ ጓደኞቻችንና ወዳጆቻችን እንዲደርስ ተደርጓል።

ከአንባቢዎች ያገኘናቸው አስተያየቶች በሙሉ የሚያስደስቱና የሚያበረታቱ ናቸው። እንደ አንዳንዶች አባባል መጽሔቱ የቀበኖችን የአብሮነት መንፈስ እንዲያንሰራራ አድርጓል። እውን መጽሄቱ በተለይ በ60 እና 70 ዓመተ ምህረቶች ውስጥ በቀበኖች መካከል የነበረን ፍቅርና ትስስር ፣ መፈላለግና መደጋገፍ እንዲያገረሽ አድርጎ ከሆነ አላማችን በአያሌው ተሳክቷል ማለት ነው። በአምናው የመጽሄቱ አዘጋጆች መልእክት ላይ እንደተዳሰሰው የመሰባሰቢያ ቀን ማዘጋጀትም ሆነ የመጽሄት ማሳተም ሀሳብ በጥቂት የተባረኩ አነሳሾች ሲጀመር ዋናው ዓላማ የቀድሞውን የቀበና ልጆች የመቀራረብና የመደጋገፍ ባህል እንዲያንሰራራ ማድረግና ትዝታችንን፣ ታሪካችንንና መልካም እሴቶቻችንን ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ፤ በተቻለም በጽሁፍ አስፍሮ ማስቀረት ነው። እስቲ ለዚህ በጎ ተግባር ቀጣይነት ተግተን ለመቆም ብርታቱን ይስጠን።

በመጨረሻም፣ አምና ጥድፊያውና የደስታ ስሜቱ ያስረሳን አንድ ዋና ነገር ነበር፤ የአዘጋጅ/ጆች ማንነት መጥቀሱን። በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነው የአምናው መጽሔት በገዛኸኝ ታደሰ ዋና አዘጋጅነት የተቀናበረ መሆኑን ለመግለፅ እንወዳለን።





# አብሮ አደጎች ምን ይላሉ?

የቀበና ተወላጆችና አብሮ አደጎች እ.ኤ.አ. ጁላይ 5 ቀን 2014 ለሁለተኛ ጊዜ በሰሜን አሜሪካ፣ በሜሪላንድ ክፍለ ሀገር፣ ሲልቨር ስፕሪንግ ከተማ ውስጥ በሚገኝ አንድ የመናፈሻ ቦታ ላይ ዓመታዊ የመሰባሰቢያ ቀን ዝግጅታቸውን አደረጉ።

ይህ በሙሉ ፍላጎትና በአብሮ አደግነት ፍቅር ላይ ብቻ የተመሰረተ ስብስብ፣ ከተለያዩ የአሜሪካ ክፍለ ሀገራት፣ ከካናዳና ከአውሮፓ፣ ቤተሰብም ያለው ቤተሰቡን ይዞ በመምጣት፣ ከአብሮ አደጎች ጋር ለመዋልና በትዝታ ወደቀበና ለመንጎድ እንዲረዳም የተዘጋጀ ነበረ።

ዝግጅቱም በጥሩ የመክፈቻ ንግግር ተጀምሮ በጉጉት ሲጠበቅ የነበረውን፣ በቀበና ፍሬዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ተዘጋጅቶ "የቀበና ማሕደር" የሚል ስያሜ ይዞ የቀረበውን መጽሔት በአድናቆት መርቆና ከፍቶ፣ ለተገኙትና በእነርሱ በኩል ለሚያገኙዋቸው አከፋፍሎ፣ በኢትዮጵያና በሌሎች ዓለማት ላሉ የቀበና አብሮ አደጎች እንዲደርስ የሚችለውን ሁሉ ጥረት እንደሚያደርግ ቃል ገብቶ ወደ ውይይት አመራ።

ልጆቹም ደግሞ በውቡ መስክ ላይ ተለቀው ሲጫወቱና ሲፈነጥዙ ለተመለከተ ምንኛ ደስታን እንደሚሰጥ መገመት አይቸግርም። የቀቤ ልጆች በዛች ዕለት አብረው ሲበሉ፣ ሲጠጡ፣ ሲወያዩና ሲሳሳቁ ተስተውለዋል።

ለብዙ ዓመታት ተለያይተው የነበሩ አብሮ አደጎች በዚያ አጋጣሚ ተገናኝተው ናፍቆታቸውን ሲወጡ ማየቱ ብቻ ከሚያስደስቱት የዕለቱ ሁኔታዎች ዋነኛው ነበር።

ይህ የደመቀ ቆንጆ ዝግጅት ከመጀመሪያው እ.ኤ.አ. የጁላይ 6 ቀን 2013 ዓመታዊ የመሰባሰቢያ ቀን ከተከናወነው ለየት ባለ መልኩ የተዘጋጀ ሲሆን፣ ማረፊያውም፣ ውይይቱም ሆነ የምግብ ዝግጅቱም የተካሄደው በአንድ ባማረ መናፈሻ ውስጥ ነበር።

በመጀመሪያው የ 2013 ዝግጅት ላይ በተለያዩ አጋጣሚዎች ሳይገኙ የቀሩ በዛ ያሉ የቀበና አብሮ አደጎች በዚህ በሁለተኛው ላይ ተገኝተዋል። የምግቡና የመጠጡ አቀራረብ፣ ጥብሳ ጥብስ ማጫጫሱን ጨምሮ፣ የሁሉንም ፍላጎት ሊያረካ በሚችል መልኩ የቀረበ ነበር። የስብሰባውን አላማ እና የወደፊቱን ዕቅድ አንተርሶ ሰፋ ያሉና ጣዕም ያላቸው ውይይቶች ተካሂደዋል።

እንግዲህ፣ "የነበሩ ይናገሩ" ነውና፣ እስቲ ከተወሰኑ የቀቤ አብሮ አደጎች ስለ ዕለቱና በአጠቃላይ የመሰባሰቡ ጉዳይ ላይ የሚሉትን እንስማ።

*"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።*

*የቀበና አብሮ አደግ ሴት፣ ወንድ፣ ልጆች ዛሬ (ጎልማሶች) የሆንን፣ ከዝንት አለም በሁዋላ፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት፣ በየሀገሩ እንደወፍ ዘራሽ ተበታትነን እየኖርን ሳለን፣ ከረጅም አመታት በሁዋላ ቸሩ አምላካችን በፈቀደው ቀንና ወቅት እያንዳንዱ ግለሰብ ራሱን ችሎ፣ ጎጆ ቀልሶ፣ ትዳር መስርቶ፣ ልጅ ወልዶ፣ ብሎም የልጅ ልጅ አይቶ በዚህ ማህበር አማካይነት ተሰባስበን ስንገናኝ ደስታዩ ወሰን የለውም።*

*ያለፉትም አባቶቻችንና እናቶቻችን፣ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ዛሬ በህይወት ከእኛ ቢለዩም፣ ታሪካቸውና ስማቸው ከእኛም አልፎ ተረካቢ በሆኑት ልጆቻችንና በልጅ ልጆቻችን ሕያው ሆኖ ሲጠራ ይኖራል።*

*በዚህ ማህበር አማካይነት መገናኘቱ ቀድሞ የነበረንን ፍቅርና አንድነታችንን ከማጠናከሩም ባሻገር ወላጆቻችን እንዴት ይኖሩ እንደነበረ ፍቅራቸውን፣ እምነታቸውን፣ ሀይማኖታቸውን፣ ወግና ባህላቸውን ልጆቻችን አያቶቻችን እንደዚህ እየኖሩ ነው ያለፉት ብለው እራሳቸውን እንዲጠይቁ ይጋብዛቸዋል።*

*ስለዚህ፣ አነሳስቶ ያስጀመረን አምላክ መድሀኒ ዐለም*

*ማህበራችንን ያጠናክርልን፣ ልጆቻችንንና ቤተሰባችንን ይባርክ፥ አይለየን። ለሦሥተኛ ጊዜም ተሰብስበን ለማክበር የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን።*

*ወስብሐት፥ ለእግዚአብሔር፥ አሜን።"*

መሠረት በቀለ በየነ
April 2015

*"በውጭ ሀገር የሚኖሩ የቀበና አብሮ አደጎች መሰባሰብ ከጀመሩ ቀደም ቢልም ለመጀመሪያ ጊዜ የሔድኩት 2014 በተደረገው የሲልቨር ስፐሪንግ ስብሰባ ላይ ነበር። በአጠቃላይ እጅግ መልካም ነገሮች የተካተቱበት ስብሰባ ነበር። በቀበና ስኖርና እንዲሁም እዚህ አሜሪካ ከመጣሁ በኃላ፣ በስም ብቻ የማውቃቸውን በርካታ ሰዎችን አግኝቻለሁ እንዲሁም ተዋውቄአለሁ። ትልቁ የስብሰባው አላማ ይህ ነበረና እጅግ የሚያስደስትና የሚበረታታ ነው። ብዙዎቹ ከወላጅ እናቴ ከአዲስ አለም እሸቴ እና ከእሱዋ ወንድሞች እና እህቶች ጋራ ያደጉ ሲሆን፣ ድሮ እንደ ታሪክ ትነግረኝ ከነበረው የልጅነት ትዝታዋ ጋር እያስታወስኩ ነበር የተሳተፍኩት።*

*በተለይ “የቀበና ማህደር” መፅሔትን ሳነብ እጅግ ነበር የተደሰትኩት። እንዲሁም የተለያዩ ፎቶዎችን ስመለከት ይህን ስብስብ ሌላ ትልቅ ትርጉም እንድሰጥ አድርጎኛል። በተጨማሪም ያደግኩበት ሰፈር የተማርኩበት ት/ቤት ማስታወሻ ለታሪክ እንደዚህ ማግኘት፣ በርቱ ግፉበት የሚያስብል ነው።*

*ይህንን ያህል ስለ መልካም ነገሩ ካልኩኝ ይበቃኛል። ለወደፊት መጨመር የሚገባው የሚመስለኝን አንድ ነገር ልበል። የስብስቡን ትርጉም ለመቀየር ወይም ወደ ሁለተኛ ደረጃ ማድረስ የሚገባ ይመስለኛል። በዚህ በአሜሪካ ስንኖር እኛ የሚገባንን ለቤተሰቦቻችንና ለቅርብ ሰዎቻችን ሁልጊዜ ማድረሳችን አልተቋረጠም። አሁን ግን ይህ ስብስብ እጅግ ጠንካራ እና ትርጉም ያለው ሆኖ እንዲቀጥል፣ አብዛኛው ተስማምቶበት፣ ረዳት የሌላቸውን የቀበና ሰዎችን ወደመርዳቱ መሸጋገር ቢቻል መልካም ይመስለኛል። የመሰባሰብ ትርጉም ከዚህ በኋላ መታየት እንዳለበት ይሰማኛል።*

*ይህ ታዲያ ሁሉንም ያሳተፈ እና ሁሉን አቀፍ የሆነ ሊሆን ይገባዋል። በእርግጥ ሁሉም የቀበና አካባቢ መረዳት የሚገባው ቢሆንም፣ ከሁሉም በጣም የባሰ ስለሚኖር፣ በዚህ ላይ ከዚህ አመት ጀምሮ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ብዬ አምናለሁ። የግድ በዚህ በመጪው አመት ወይም ሁለት አመት መጀመር ባይገባውም፣ በምን መልኩ መርዳት እንደምንጀምር ማተኮርና ማቀድ የሚገባ ነው።*

*የእስከአሁኑ ሒደት እጅግ የሚያስደስትና የሚያበረታታ፣ ለወደፊት ትርጉም ያለው ትልቅ ታሪክ ጥሎ ለሚያልፍ በጎ ነገር መሰረት የጣለ መሰባሰብ ነው ብዬ አምናለሁ። እንግዲህ ሁላችንም እንዳለን ያቆየንና ለ2015 የመሰባሰቢያው ቀን ያድርሰን። ሌት ተቀን ደከመኝ ሳይሉ ለሚሰሩት አሰባሳቢዎች በአጠቃላይ ብርታቱን ሁሉ ይስጣቸው እላለሁ።"*

ቴዎድሮስ እሸቴ ወልደማርያም
May 2015

*"በቅድሚያ ቀበና ላፈራቸው ፍሬዎች ወይም አብሮ አደጎች ስመኘው የነበረውን ራዕይ ባልተጠበቀ ሰዓት ጊዜውን ጠብቆ እንደ አደይ አበባ ፈክቶ ስላየሁትና በፍቅር ላገናኘን አምላክ ክብር ምሥጋና ይግባው። የተወለድኩበትን፣ ሮጬና ፈንድቄ ያደግሁበትን፣ ኳስ ያንከባለልኩበትን፣ ቡሄ የጨፈርኩበትን መንደር ለቅቄ ከወጣሁ 40 ዓመታት ቢያልፋም ትዝታው ግን አብሮኝ አለ። ከአብሮ አደጎቼ መካከል ምንጊዜም ከህሊናዬ የማይጠፉት ዛሬ በሕይወት የሌሉት አቶ ተዘራ ተፈራና አቶ አዝመራ ሐድጎ ናቸው፡፡ ከእነዚህ አብሮ አደጐቼ በተገናኘን ቁጥር ሁልጊዜ የምንወያየው የቀበና ማኅበር ማቋቋምን ነበር፡፡ እነሱ ለማየት ባይታደሉም ይኸው ዛሬ ራዕያቸውን እውን አድርጋችሁታል፡፡ ይህን የተቀደሰ የቤተ ሰብ ማኅበር በማየቴ በጣም ተደስቻለሁ፡፡"*

ጌታቸው በላይነህ (ዶ/ር)
Novemeber 2014


ካምናው የመሰባሰቢያ ቀን ውሎ

እነሆ የቀበና ተወላጆችና አብሮ አደጎች ይህንን በመሰለ ጣዕም በተሞላው ዝግጅት ቀናችንን አሳልፈን፣ ለታሪክ የሚቆዩ የፎቶግራፍና የቪዲዮ ቀረፃዎችን አካተን፣ አይቀሬው ሰዓት ደረሰና ወደ አመሻሹ ላይ አንገት ለአንገት እየተቃቀፍን በፍቅር ተመሰጋግነንና ተመራርቀን ተሰነባበትን፡፡ የከርሞ ሰው ይበለን ተባብለንና ተሳስመንም ተለያየን፡፡

ይኸው ከርሞም ዘንድሮ ሆነና ለሶስተኛ ጊዜ ልንሰባሰብ ነው፡፡

# የልጆች ዓምድ

በዚህ የመጽሔቱ ክፍል ልጆቻችን የሚጻጽፉትን የምናቀርብበት ይሆናል። ለዚህ ዕትም ሁለት ወጣቶች የሚሉት አላቸው። እጹብና እየሩሳሌምን ለተሳትፏቸው እያመሰገንን፤ ሌሎችን ለሚቀጥለው እንጋብዛለን።

## My Ethiopian Heritage



Born to Ethiopian parents in the land where the explorer Jacques Cartier first set foot, I am a Canadian and Ethiopian by heritage. Being a Canadian of Ethiopian origin means sharing the characters of two nationalities. My identity is woven from the elements of a modern new world, on the one hand and a traditional and proud ancient country, on the other.

My Ethiopian heritage is manifested in many different ways. For example, I have this constant craving for delicious Injera and any spicy wot, especially I have an everlasting love for Shiro. Also, I have this natural ease to recognize and connect with other Ethiopians.

Sometimes, I feel like a complete Canadian. Other times, I feel like a real Habesha. These feelings may be considered as contradictory; but they are not. They are expression of my belongingness to two different cultures that co-exist inside me and make up my identity. I always know that underneath my characters that I acquired from my birth place, I possess unfading Ethiopianness.

My little brother and I always remember our roots, Ethiopia, where our parents came from. We are lucky to have visited Ethiopia a number of times, and each time we returned with fond memories. We truly value our Ethiopian heritage no matter the environmental pressures that force us to be oblivion about it.

Etsub Worku Damena (Ethiopian style) OR
Etsub Worku Yifru (Canadian style)




# A Tale of two Cultures

It was the day of my graduation party. My parents had done EVERYTHING for me. The venue looked perfect, the food was mouthwatering, and my mom even had a cute table set up for my high school friends. I was so excited, because this was the first time that a lot of my friends would meet my extended family.

In the midst of all of the preparation, I saw my uncles haul in a large wooden fixture. It kind of looked like a swing set without the swings. My eyes immediately widened. It just hit me. There was going to be a huge, raw, hanging cow leg at my graduation party. How was I going to explain this to my friends?! They were going to think that we were a bunch of amateur butchers who were too lazy to cook our own meat! I look back on that day and think about how naïve I was. My friends didn't care; they embraced the culture and I should have followed their lead. Some of them even tried the tirey siga (ጥሬ ስጋ) and went back for seconds.

Don't get me wrong, I experienced a lot of culture shocks between my Habesha norms and American ones. My siblings and I were always expected to be the best hosts, a "B" was never as good as an "A", and the consequences were much more personal. Don't even get me started on how much Febreeze I would spray in order to cover up the smell of itan (ዕጣን) when my friends were on their way over.

Identifying as an Ethiopian American while growing up was a kind of confusing. I knew what Ethiopians valued, I knew what Americans valued, but I didn't know what I valued. Now that I am older, I feel like I have a more accurate description. I am a teacher who sets very high expectations for my students, I keep up with my "A"s in graduate school. I am told that I always make people feel welcomed, I force my parents to only speak to me in Amharic, and while I am not yet a fan of tirey siga, my love for kitfo (ክትፎ) is unwavering. My Ethiopian heritage is what has shaped me into who I am today and I could not be more THANKFUL for that.



Eyerusalem Solomon



# እስቲ እናስታውሳቸው

በመጀመሪያው የመጽሄታችን ዕትም ላይ እንደተገለጸው፣ ይህ ክፍል በተለያዩ ጊዜያትና ምክንያቶች ከዚህ ዓለም ያለፉትን፣ ለመጨረሻው የተለዩንን የቀበና ማህበረሰብ አባላትን የምናስብበት ነው።

ብዙዎቻችሁ እንደምታውቁት በቅርቡ ከተለዩን ወገኖቻችንና አብሮ አደጎቻችን ውስጥ አቶ ጌታቸው በቀለ፣ መምህር ካሳሁን ሚደቅሳ፣ ሠይፈ አበበ፣ ኒሻን ኃይሌ፣ ምንትዋብ የማነ፣ ንጉሱ ተስፋዬ፣አለማየሁ በርይሁን፣ፍቃዱ ተፈራ እና ሚሚ በፍቃዱ ይገኙበታል። እግዚአብሄር እነርሱንና ሌሎችንም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩንን ወገኖቻችንን ሰላማዊ እረፍት እንዲያደርግላቸው፣ ለቤተሰቦቻቸውና ወዳጆቻቸውም መጽናናትን እንዲሰጣቸው እንለምናለን።

በዚህ ዕትም ባለፈው ዓመት የጀመርነውን በመቀጠል፣ በደርግ ዘመን በፖለቲካ አቋማቸው የተነሳ በወታደራዊው መንግስት የተገደሉትንና ባለፈው ዓመት ዕትም አጭር የህይወት ታሪካቸውን ከፎቶግራፋቸው ጋር ያላቀረብናቸውን ወንድሞቻችንን እንዘክራለን።

ዘንድሮም እንደ አምናው ሁሉ የእነዚህ ወንድሞቻችንን ፎቶዎችና አጭር የህይወት ታሪካቸውን የሰማዕታቱን ቀሪ ዘመዶች ወይም የቤተሰብ አባላት አፈላልጎና አማክሮ ማሰባሰቡ ትዕግሥት የተላበሰ ጥረትን የሚጠይቅ ነበር። ከዚህ ቀጥሎ ካቀረብናቸው የወንድሞቻችንን የመታሰቢያ ሰነዶች ውስጥ የተወሰኑትን በማሰባሰብ በኩል፣ ዘንድሮም ወንድማችን አሰፋ ለገሠ የተጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። አሴ ! እናመሰግናለን።




በዚህ ዓምድ መጨረሻ ላይ ማንነቱ ባልተገለጸ ሰው (anonymous) የተጻፈ ግጥም ጨምረን አቅርበናል። ግጥሙ በኢትዮጵያ ውስጥ በ 1970ዎቹ ውስጥ በወታደራዊው መንግሥት የተካሄደው ግድያ፣ እስራትና ማሳደድን ተከትሎ በስፋት መከሰት የጀመረው የኢትዮጵያውያን ስደት ያስከተለውን ግለሰባዊና ማህበረሰባዊ የስነ ልቦና ምስቅልቅል ይዳስሳል። ጽሁፉ በአቀራረቡ አንድ ሰው ከራሱ ጋር የሚያደርገውን ሙግት ያሳያል። በዚያ አስከፊ ዘመን ውስጥ ያለፈ አንድ ኢትዮጵያዊ ከዓመታት በኋላ በዚያ ምስቅልቅል ውስጥ የተለየውን አብሮ አደግ ጓደኛውን ቢያገኘው ምን ሊነግረው እንደሚገባ ወይም እንደሚሻ ራሱን ይጠይቃል።

## በሉ እስቲ አብረን እናስታውሳቸው !





## ወንድማገኝ ብርሃኑ (1946 -1971)

ወንድማገኝ ብርሃኑ በሰፈር ቅጽል ስሙ "ውርዬ"ከአባቱ ከሃምሳ አለቃ ብርሃኑ ተሰማ እና ከእናቱ እማሆይ ብርሃኔ ዉቤ በ1946 ዓ.ም ተወለደ። በኢትዮጵያ አብዮታዊ እንቅስቃሴ እንደተጀመረ፣ በ1967 ዓ.ም ትምህርቱን አቋርጦ ስሜቱ ወደ አዘነበለበት የአየር ወለድ ሠራዊት ውስጥ ለማገልገል ተቀጠረ። በሰራዊቱም የኮማንዶ ስልጠናውን ተከታትሏል፣ አምስት ጊዜ ዝላይ በመፈጸምም ተገቢውን የብቁነት ማረጋገጫ ምልክት (ዊንግ) አግኝቷል።

ወንድማገኝ በነበረው የህዝብ ፍቅር፣ የወታደራዊውን የደርግ አገዛዝ ጸረ ሕዝብነት በመገንዘብና ሥርዓቱን በመቃወም የሚያፈቅረውን የአየር ወለድ ጦርን በመክዳት ከተወሰኑ የሙያ ባልደረቦቹ ጋር በመሆን ተሰወረ። በዚህም የተነሳ፣ ደርግ በአዲስ አበባ ከተማ በየቀበሌው ፎቶግራፉቸውን በመለጠፍ ከፍተኛ ፍለጋና ክትትል ከሚያደርግባቸው የህዝብ ልጆች አንዱ ሆነ። ከክትትሉ ለማምለጥና ሕዝባዊ ፍቅሩን የበለጠ መወጣት ያስችለኛል ብሎ ባመነበት መሰረት፣ በወቅቱ የደርግን መንግሥት በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ግዛቶች በመሣሪያ ይፋለሙ ከነበሩት ኃይሎች አንዱ የነበረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ) በዚያ ለጋ ዕድሜው በመቀላቀል ጭቁኑን ህዝብ ከፋሽሽታዊው ወታደራዊ አገዛዝ ነፃ ለማዉጣት መታገሉን ተያያዘው። በኢሕአሠ ውስጥም የአየር ወለድ ልምዱን ለጎዶቹ በማካፈልና ሠራዊቱን በማሰልጠን፣ እንዲሁም በተለያዩ አውደ ውጊያዎች በመሰማራት ደርግን ተፉልሟል።

"የአሲምባ ፍቅር" በሚል ርዕስ ተዘጋጅቶ የቀረበው መጽሀፍ ደራሲ ካሕሳይ አብርሃ እንደገለጸው፣ ዘመናዊ ኤምፎርቲን ጠመንጃ ታጥቀዉ አርባ የሚደርሱ አየር ወለድ አባላት ከኢሕአሠ ጋር ለመቀላቀል ምድረባ ላይ አቀባበል ሲደረግላቸው ልዩ ድባብና ግርማ ተላብሰው ከነበሩት ውስጥ ወንድማገኝ አንዱ ነበር፤ ይልና ታሪኩን ሲቀጥል፤ የእነርሱ ወደኛ ድርጅት መግባት በድርጅታችን እንድንኮራ፣ በአቋማችን እንድንተማመንና እንድንፀና የሚያደርግ መንፈስ እንድንላበስ አድርጎን ነበር ይላል።

በአስማማው ኃይሉ ተደርሶ በ 2006 ዓ.ም. ለንባብ በበቃው "ኢ.ሕ.አ.ሠ. ቁጥር ሁለት" መጽሀፍ በምዕራፍ 3፥ገጽ 35 ላይ እንዲህ ይላል፤ "በ1971 አጋማሽ ደርግ በበጌምደር አድርጎት በነበረው መጠነ ሰፊ ወረራ ... በሁለት መደበኛ ክፍለ ጦርና አያሌ የአርሶ አደር ጦር ዘማቾች ኢሕአሠን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ዘምተዋል። የሪጅን ሁለት የኢሕአሠ ሠራዊት ግን ለሃያ ሶስት ቀናት ያህል በቆራጥነት ተዋግቶ መልሶታል። በዚህ ጦርነት አያሌ የጠላት ወታደሮች በመጎዳታቸው ወደፊትም ሊገፉ ባለመቻሉ የጦር አይሮፕላኖችም ተጠቅሞ ነበር ... በመከላከሉ ጦርነት የኃይል መሪው ወንድማገኝና የኃይል ኮሚሳሩ አበበ አተባ መስዋዕትነት ከከፈሉ ጀግኖች መካከል ጥቂቶቹ ነበሩ።"

ለአባት እናቱ፣ ለእህት ወንድሞቹ፣ በአጠቃላይ ለአብሮ አደጎቹና ለጓዶቹ ጥልቅ ፍቅር የነበረው ወንድማገኝ በማንም የመወደድ ፀጋንም የተላበሰ ለግላጋ ወጣት ነበር።

የቆራጡ ታጋይ የወንድማገኝ ብርሃኑ ታሪክ ህያው ሆኖ ለዘላለም ሲታወስ ይኖራል።



ፀጋዬ ቶሎሳ ከእናቱ ከወ/ሮ አበበች በየነ እና ከአባቱ ከአቶ ቶሎሳ ሙለታ መስከረም 5 ቀን 1948 ዓ ም ቀበና፣ ኮሪያ ሰፈር ተወለደ።

ፀጋዬ ለእናቱ የመጀመሪያ ልጅ ለአባቱ ደግሞ አራተኛ ልጅ ነበር። በአባትና እናቱ፣ በወንድምና እህቶቹ፣ እንዲሁም በመላው የአካበቢው ማህበረሰብ ተወዳጅ ነበር። ከአብሮ አደጎቹ ጋር ውሃ ተራጭቶና ኳስ ተጫውቶ ያደገ ሲሆን፤ በተረትና በፊልም ያገኛቸውን ታሪኮች አሻሽሎና አዝናኝ በሆነ መልኩ በማቅረብ የሚታወቅና የሠፈር ጓደኞቹ አብረውት ለመሆን የሚመርጡት፣ የሚናፍቁት ወጣት ነበር።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በኮከበ ጽባህ ት/ቤት ተከታትሏል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱንም በዚያው ትምህርት ቤት በመከታተል ላይ ነበር። ፀጋዬ በስፖርት እንቅስቃሴም የተሳካለት ነበር። በትምህርት ቤት ለክፍሉ በግብ ጠባቂነት ተሰልፎ በመጫወትና በችሎታውም ዝነኛ ነበር።

ከሠፈር አብሮ አደጎቹ ጋር "ቃኘው በኮሪያ የስፖርት ክለብ" ውስጥ አባል የነበረ ሲሆን በእግር ኳስ በግብ ጠባቂነት እንዲሁም በድምጻዊነት ጓደኞቹንና ማህበረሰቡን በማዝናናት ይታወቅ ነበር። ተደርሰው የሚሰጡትን ልዩ ልዩ ዜማዎች በማንጎራጎርና በአዝናኝነቱ ይታወሳል።

ኢትዮጵያ በወታደራዊ አገዛዝ ስር እንደገባች እንደማንኛም የአካባቢውና የአገሪቱ ወጣቶች ሁሉ ለህዝባዊ መንግሥት መቋቋም ድምጹን ማሰማት ጀመረ። መጋቢት 14 ቀን 1969 ዓ. ም. በአዲስ አበባ ከተማ አቀፍ አሰሳ በተጀመረበት ዕለት በሰፈር ውስጥ በጓደኛው ቤት እንዳለ ለአሰሳ የመጡ የአካባቢው የአብዮት ጥበቃ አባላት እርሱንና ጓደኛውን ይዘው ወደ አንደኛ ፖሊስ ጣቢያ አሳልፈው በመሰጠታቸው እስከ ሰኔ 3 ቀን 1969 በእስር ቆይቶ ተፈታ።

ከዚያም ሐምሌ 11 ቀን 1969 ዓ. ም. ምሽት ላይ የደርግ አፋኝ ስኳዶች ከቤቱ ሊይዙት ሲሉ አምልጦ በመውጣት በተለያዩ የአዲስ አበባ አካባቢዎች ተደብቆ ይኖር ነበር። ይሁንና ከጥቂት ጊዜ በኋላ የአካባቢውን ወጣቶች በመከታተል መግቢያ መውጫ አሳጥተውት በነበሩት አረመኔዎች፣ በከፍተኛ 13 ቀበሌ 06 የአብዮት ጥበቃ አባላት እጅ ወደቀ። አራት ኪሎ አካባቢ ተይዞ፤ ወደ አስከፊው ማዕከላዊ እስር ቤት ተወረወረ።


የቤተሰቡ አባላት ለጥቂት ጊዜ ሲጠይቁት ቢቆዩም እንደተለመደው አንድ እሑድ ቀን ምግብ ለማቀበል እስር ቤቱ ሲደርሱ ምግባችሁን አንቀበልም ሁለተኛ ወደዚህ ጣቢያ እንዳትደርሱ የሚል ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው። ያ ምላሽ በዘመኑ አሠራር ልጃችሁ በህይወት የለምና ከእንግዲህ ወደ እስር ቤቱ በመምጣት አታስቸግሩ ማለት ነበር። ፀጋዬ ከደረሰበት አስከፊ ግርፋትና ስቃይ በማገገም ላይ እያለ በ 1970 ዓ.ም. ታህሣስ ወር ውስጥ ከማዕከላዊ እስር ቤት አውጥተው ወሰዱት። አልተመለሰም። የቀይ ሽብር ሰለባ ሆነ።

ወጣት ፀጋዬ ቶሎሳ በሚኖርበት አካባቢ ለሚያውቃቸው ጎስቋሎች፣ ብሎም ለመላው የኢትዮጵያ ላብ አደርና አርሶ አደር የተሻለ ዘመን እንዲመጣ ከመመኘትና ከመጣር በስተቀር ጥፋት አልነበረውም። ለተሻለች ኢትዮጵያ በመቆማቸውና በመዘመራቸው ብቻ፣ በደርግና ግብረ አበሮቹ የቀይ ሽብር ሰይፍ በለጋ ዕድሜአቸው ከተቀጠፉት በሺዎች የሚቆጠሩ የዚያ ዘመን፣ የዚያ ትውልድ አባላት አንዱ ነበር።



**ፀጋዬ ቶሎሳ (1948 - 1970)**





አማኑኤል ሣህለ ማርያም (1952 – 1970)

አማኑኤል ከአባቱ ኮለኔል ሣህለ ማርያም ፍጌና ከእናቱ ወይዘሮ አሰለፈች ቦጋለ ግንቦት 1952 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ተወለደ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት በመከታተል ላይ እንዳለ ነበር፤ ምቹ ህይወቱን ትቶ ላልተመቻቸው ኢትዮጵያውያን የተሻለች አገርን የመፍጠርን ዓላማ ሰንቆ ወደ ፖለቲካዊ ትግል የገባው። እንደ ሌሎች የዕድሜ እኩያዎቹ እርሱም ለአገሩ በጎ ነገር በማሰብ የተሻለ ሥርዓት ይመጣ ዘንድ ገና በለጋ ዕድሜው የተቻለውን ማድረግ ጀመረ። በዚህ የተነሳም የአካባቢው ባለሥልጣናት እርሱን ብቻ ሳይሆን ቤተሰቡንም መከታተልና ማስጨነቁን ተያያዙት። መጋቢት 14 ቀን 1969 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ አቀፍ የቤት ለቤት አሰሳ በተጀመረበት ዕለት እርሱንና የተወሰኑ የቤተሰቡን አባላት ከቤታቸው ወስደው አሰሯቸው።

አማኑኤል ከመጀመሪያው እስራቱ ቢፈታም በአካባቢው የአብዮት ጥበቃ አባላት ክትትል የተነሳ ሰላማዊ ኑሮ መምራት ስላልቻለ ከቤቱ ተሰዶ በአዲስ አበባ የተለያዩ ሥፍራዎች ተደብቆ መኖር ተገደደ። ያም ሆኖ ከአሳዳጆቹ ሰይፍ ማምለጥ አልቻለም፤ በ 1970 ዓ.ም. መጀመሪያ አካባቢ በዚያ ለጋ ዕድሜው በቀይ ሽብር አረመኔአዊ በትር ተቀጨ።

አማኑኤል ብሩህ አእምሮና ጨዋ ሥነ ምግባርን የተላበሰ እጅግ ተወዳጅ ወጣት ነበር። በልጅነቱ በኢትዮጵያ ወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማህበር (ወ.ወ.ክ.ማ) ውስጥ በተለያዩ እንቅስቃሴዎች አዘውትሮ የሚሳተፍ፣ በተለይም በጠረጴዛ ኳስ ጨዋታ የላቀ ችሎታ የነበረው እንቡጥ ታዳጊ ነበር።

ዐመለ ሸጋውና የህዝቦች አርነት ታጋዩ አማኑኤል በእህቶቹና ወንድሞቹ፣ በጓዶቹና በኢትዮጵያ ለፍትሃዊ ሥርዐት በተደረገው ታሪክ ውስጥ ሁሌም ሲታወስ ይኖራል።



ሞገስ ማሞ (1951 – 1970)

ሞገስ ከአባቱ ከአቶ ማሞ ወልጻድቅ እና ከእናቱ ከወይዘሮ ወይንሸት ተክለመድህን በ1951 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ።

ሞገስ የወጣትነት ጊዜያቸውን ብሎም ህይወታቸውን ለአገራቸው ከገበሩት የቀበና ልጆች አንዱ ነበር። ገና በልጅነቱ ነበር አገሩን ማገልገል የጀመረው። በመጀመሪያ የቀድሞው የኢትዮጵያ ባህር ኃይል ባልደረባ በመሆን፣ በኋላም ወታደራዊ አገዛዝ ለአገሪቱ አይበጅም በማለት ሥርዓቱን በመፋለም። በባህር ኃይልነቱም ሆነ በኢሕአፓ ታጋይነቱ የሞገስ የዓላማ ጽናትና ቆራጥነት ለሌሎች በትግሉ ውስጥ ለነበሩ ጓዶቹ ሁሉ ኃይልና ምሳሌ ነበር። በአደጋ የተሞሉ ወታደራዊም ሆኑ ፖለቲካዊ ሥራዎችን ለማከናወን ከፊት ይሰለፉ ከነበሩት ሞገስ አንዱ ነበር።

ሞገስ በደርግ የጸጥታ ኃይሎች እጅ የወደቀው ከጓዱ ከበለጠ አየለ ጋር ሆኖ ነበር። በአስከፊው የማዕከላዊ እስር ቤት በእስርና በምርመራ ስቃይ ሲደርስበት ቆይቶ በ1970 አመተ ምህረት መጀመሪያ አካባቢ ተገደለ። በለጠም በተመሳሳይ ምሽት በወታደራዊው መንግስት ገዳዮች ከእስር ቤት ተወስዶ በጭካኔ እንደተረሸነ ይገመታል፤ ሁለቱም አብረው እንዳደጉ፣ አብረው ፍትህ አልባ ሥርዓትን እንደታገሉ፣ አብረው ለዘላለም አንቀላፉ። እንደ በለጠ ሁሉ ሞገስም ለገዳዮቹ ከህዝብና ከታሪክ ፍርድ እንደማያመልጡ፣ የማታ ማታ ህዝብ አሸናፊነቱ እንደማይቀር እየነገራቸው ነበር ህይወቱ ያለፈው።

የቆራጡ ታጋይ የሞገስ ማሞ ስምና ታሪክ ህያው ሆኖ ይኖራል።



## በለጠ አየለ (1953 - 1970)*

ወጣት በለጠ ከአባቱ ከአለቃ አየለ እንየውና ከእናቱ ከወይዘሮ አዳም ተመስገን ጥቅምት 9 ቀን 1953 አመተ ምህረት ቀበና፣ ኮርያ ሰፈር ተብሎ በሚጠራው ቦታ ተወለደ። እድሜው ለትምህርት ሲደርስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በእድር ትምህርት ቤት ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ድረስ ተከታትሏል። ከዚያም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪ እያለ ነበር በአገራችን ላይ ያንዣበበው የፋሽስቶች መንግስት በህዝብ ላይ የሚያደርሰውን የግፍ በደልና ጭቆናን በመቃወም የተነሳው።

በለጠ ለነፃነት ለመብትና ለህዝባዊ መንግስት መቋቋም ከሚታገለውና ህዝባዊ ከሆነው ከኢሕአፓ ጎን ሆኖ በመታገልና በማታገል ግዴታውን በመወጣት ላይ እንዳለ በደርግ ታጣቂዎች በ1969 ዓ.ም. መጨረሻ አካባቢ በጥይት ተመቶ ተያዘ።

በታሠረበት ፖሊስ ጣቢያ ለሳምንታት በግርፋትና በድብደባ ቢያሰቃዩትም ከባድ ጉዳት ቢያደርሱበትም ከዓላማው ፍንክች ሳይል ፋሽስቶችን እያወገዘ ድል የህዝብ ነው እያለ አሰቃቂ ምርመራቸውን ተቋቁሟል። "የትግሉ ነው ህይወቴ"ን እየዘመረ ነበረ በአረመኔዎቹ እጅ በ1970 አመተ ምህረት መጀመሪያ አካባቢ በ17 ዓመቱ የተገደለው።


በለጠ በአላማው ፅኑ እምነት የነበረው ቆራጥ፣ ሀገሩንና ወገኑን ወዳድ ወጣት ነበረ። በለጠ እና ጓዶቹ ለፍትህና ለዴሞክራሲ ያሰሙት ድምፅና የከፈሉት መስዋዕትነት ስማቸው ከመቃብር በላይ በታሪክ ሲታወስ እንዲኖር ያደርገዋል።

መምህር ሀብታሙ ከአባቱ ከአለቃ አየለ እንየውና ከእናቱ ከወይዘሮ አዳም ተመስገን ጥቅምት 5 ቀን 1947 ዓመተ ምህረት ተወለደ። እድሜውም ለትምህርት ሲደርስ በኮከበ ጽባሕ የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቋል። ከዚያም ከመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም ተመርቋል።

ሀብታሙ በጎንደር ክፍለ ሀገር በደባርቅ አውራጃ በአስተማሪነት ተመድቦ ያስተምር ነበር። የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባል ሆኖ በወቅቱ በሀገራችን ይካሄድ የነበረውን ህዝባዊ እንቅስቃሴ በመደገፍ እና ወታደራዊውን የአምባገነን መንግስት ለመጣል በተደረገው ትግል ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል።

ሀብታሙ ከህዝብ ጎን በመቆሙ በክፍለ አገሩና የአካባቢው ሹማምንት ክፉ ዐይን ውስጥ ገባ። በ 1969 ዓ.ም. መጨረሻ አካባቢ ተይዞ በእስር ከቆየ በኋላ በ1970 መጀመሪያ ላይ በጎንደር የደርግ ከፍተኛው ባለሥልጣን በሻለቃ መላኩ ተፈራ መሪነት በስፋት ይካሄድ በነበረው የቀይ ሽብር ሰለባ ሆነ።

ሀብታሙ በሰፈራችን ውስጥ በሰው አክባሪነቱ፣ በታዛዥነቱ፣ በሩህሩህነቱና ለሰው ባለው ፍቅር ይታወቅ ነበር። እግር ኳስ መጫወት የሚወድ፣ በትምህርቱም ጎበዝና ታታሪም ነበር። ሀብታሙ አየለ ለኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነትና ለፍትህ ውድና ክቡር ህይወታቸውን በወጣትነታቸው ከከፈሉት የቀበና ልጆች አንዱ ነበር።



ሀብታሙ አየለ (1947 - 1970)*

*የሀብታሙና የበለጠ አጫጭር የህይወት ታሪኮች ‘ከቀበና ማህደር’ ቁጥር 1 ላይ ወጥተው የነበሩ ቢሆንም አንዳንድ ግድፈቶችን ለማረምና ከፎቶአቸው ጋር ለማቅረብ ሲባል በድጋሚ ታትመዋል፤ ምንም እንኳን ከነዚህ የተሻሉ ፎቶዎችን ማግኘት ባንችልም።

# ያንን አብሮ አደጌን፤ ምን ብዬ ልንገረው?

የልጅነት ወጉን የእኛን ነገር ትተን
የህብረተሰቡን ያገር ጉዳይ ይዘን
ፖለቲካ አንስተን፤ ፖለቲካ አጥንተን
ጫት አንድ ላይ ቅመን ሲጋራ ተካፍለን
ለጭቁኖች አዝነን ሀብታሞችን ጠልተን
ባንድ ፍልስፍና፤ ባንድ አመለካከት
ላንድ ዓላማ ቆመን
በትግሉ መድረክ ላይ እፊት ተሰልፈን
አንዱን ስንቃወም ሌላውን ደግፈን
ይሙት ይውደም ብለን፤ ይኑርልን ብለን
ደጋፊ ፈልገን
የእኛን ፍልስፍና ለማስፋት ፈልገን
ጥናት ክበብ ፈጥረን ሌላ ሰው መልምለን
ማታ ለውይይት ሌሎች ሰዎች ጋብዘን
ለሲጋራ መግዣ ለጫት ገንዘብ አጥሮን
ሰዓት ልብሳችንን ሃራጅ ብለን ሸጠን
ድሮም የኛ አይደለም የህዝብ ነው ብለን
ሥርዓት ልንቀይር ከእኛ ልንጀምር
የእኔ የሚባል ትተን
ሁሉንም አክብረን
ሴት መልከፍ አቁመን
እህት ጓዲት ብለን
በረንዳ ቁጭ ብለን ከኩሊው አውርተን
ንቁ ተደራጁ ተባበሩ ብለን
ድሉ የህዝብ ነው እናቸንፋለን
የኛን እንጉርጉሮ መዝሙራችን አርገን
የኢትዮጵያ ጭቁኖች ከዓለም ጭቁን ጋር
ዘመድ ናቸው ብለን
ከዓለም ፈላስፋዎች ብዙ ትምህርት ወስደን
የብዙ ሀገር ትግል ተሞክሮ አጥንተን
ቀይ ባንዲራ አንስተን መፈክር አንግበን
ህዝብ ለመቀስቀስ ሰልፍ ቦታ ሄደን
አብረን ተሰልፈን መዝሙር አሰምተን
ወታደር መጥቶብን፤ ጥይት ተኩሶብን
በጥይት በትናን
ከዛ ቀን ጀምሮ ሳንገናኝ ኖረን
ሃያ አመት አልፎ፤ ሰላሳ አምስት ሆኖን
ያንን አብሮ አደጌን፤ ያንን ጓደኛዬን
ብቻዬን ብቻውን አንድ ቀን ባገኘው
ሳስበው ጨነቀኝ
ምን እንደሚነግረኝ፤ ምን እንደምነግረው
ያንን ጓደኛዬን፤ ያንን አብሮ አደጌን ገና ሳላገኘው
ነገሩ አሳስቦኝ በሃሳቤ አግኝቼው
የት እንደነበረ ቀድሜ ጠይቄው።
ማን ምን እንደሆነ የት እንደደረሱ
ያየውን ለማውራት ቅድሚያ ዕድል ሰጥቸው
ያን ጊዜ ሰልፍ ላይ ጥይት እኔን መቶኝ
ወድቄ ተኝቼ ወታደር አግኝቶኝ
እስር ቤት ወስደውኝ፤ ከርቸሌ ልከውኝ
አስር ዓመት ሙሉ ማንም ሰው ሳያየኝ
ፍርድ ቤት ሳልቀርብ፤ ሳይፈረድብኝ
ይግባኝ ሳልሰማ ምስክር ሳላገኝ
ከአስር አመት በኋላ ነው፤ በምህረት የፈቱኝ
ምክንያትም የለው ለምን እንዳሰሩኝ
ለምን እንደፈቱኝ
ስህተት ነው ብለው መድህንም አልሰጡኝ።
ብሎ በማፌዝ ሳቅ፤ ፈገግ ብሎ አስቆኝ
ጸጉሩ መመለጡን፤ መንጣት መገርጣቱን
ጎንበስ ብሎ አሳየኝ።
እንዳጎነበሰ ያለፈው ትዝ አለው
ዐይኑ ደም ለበሰ ሰውነቱን ሞቀው።

እነ እንትና ደግሞ ላመኑበት ቆመው
ባመኑበት ጸንተው
ስልጣን ሳይጠማቸው
ስልጣን ሳይሸታቸው
ወይ ሳይሸሹ ፈርተው
ታግለው ሊያታግሉ ምንም ሳይታክቱ
እትግሉ መድረክ ላይ የጀግና ሞት ሞቱ።

እነ እንትና ደግሞ እጃቸውን ሰጥተው
ጠቁመው አስይዘው
ስልጣን ተቀብለው ስልጣን ተሸልመው
እዛው አራት ኪሎ ትልቅ ቦታ አላቸው።

እነ እንትና ደግሞ፤ ደኸኛው ሲፈርስ ለዛኛው ገብረው
ለጊዜውም ቢሆን ስልጣን ተቀብለው
በኋላ ተይዘው አራት ኪሎ ሄደው
ባርጩሜ ተገርፈው
ኑሮን ይገፋሉ በጣም ተደብረው
መስከረም ሁለት ላይ ከእስር ተለቅቀው።

እነ እንትና ደግሞ ያንኪ ጎ ሆም ያሉት
ያንኪ ሀገሩ ሲሄድ
ያሳደዱ መስለው ተሰደው የቀሩት
እውጭ መሆናቸው አልፎ አልፎ ቢወራም
ምን እንደሚሰሩ ምን እንደሚያስቡ የሰማነው የለም።
በኔ በኩል ያለው ባጭሩ ይሄ ነው
እስኪ አንተ ንገረኝ
ምን አስባችኋል ወደፊቱ እንዴት ነው?
ብሎ ቢጠይቀኝ
ያንን ጓደኛዬን ምን እንደምነግረው
ሳስበው ጨነቀኝ።

ምንም ሳልደብቀው
ልነግረው ያሰብኩት ባጭሩ ይኸ ነው።
እንትናና እንትና ሱዳን ተገናኝተው
ትግሉ ከፈረሰ እንጋባ ብለው
እሷ ፈርማለት እሱም ፈርሞላት
ግሪን ካርድ የሚባል ወረቀት አውጥተው
እዛው አሜሪካ ፈረንጅ አገር ናቸው።

እነ እንትና ደግሞ ያንኪ ጎ ሆም ያሉት
ያንኪ ሀገሩ ሲሄድ ያንኪን ተከትለው
ያንኪ ሀገር የሄዱት
ዛሬ ከያንኪ ጋር ለመኖር ተስማምተው
እዛው አሜሪካ ፈረንጅ ሀገር ናቸው።

እነ እንትና ደግሞ ታክሲ ነጂ ሆነው
እነ እንትና ደግሞ የመኪና እረኛ ጠባቂዎች ሆነው
ገንዘብ አጠራቅመው
ሱቅና ምግብ ቤት፤ ጋዝ ስቴሽን ከፍተው
እዛው አሜሪካ ፈረንጅ ሀገር ናቸው።

እነ እንትና ደግሞ ፍልስፍና ትተው
ቁጥርና ሳይንስ የሞተር አሰራር
የህንጻ ግንባታ ኤሌክትሪክ አጥንተው
በየመስሪያ ቤቱ መሃንዲስ ተብለው
ፖለቲካ ነገር ሰው ሲያነሳባቸው
እንዳልነበሩበት እንዳልሰሙ ሰምተው
እዛው ባህር ማዶ ፈረንጅ ሀገር ናቸው።
እነ እንትና ደግሞ ዛሬም እንደ ድሮው
ቆሽሽ ያለ ለብሰው
ፖለቲካ ነገር ሁልጊዜም ቢያወሩት
ቃላት አለወጡም፤ ሃሳብ አልጨመሩም።
ስላለፈው ውድቀት እውነቱን አውጥተው
ታሪኩን አልጻፉም
ለወደፊቱም ታሪክ ሰሪ አይደሉም

ሰዓቱ እየሄደ እድሜያቸው ቢገፋም
ጊዜ ወርቅ አይደለም እነሱ አይቆጥሩትም።
ለወሬ የሚመች ሰፊ ሀገር ነው ብለው
እዛው ባህር ማዶ ፈረንጅ ሀገር ናቸው።

እነ እንትና ደግሞ ባለፈው ድርጅት
በትግሉ ተናደው
ድሮም ማዕበሉ ነበር የያዛቸው
ዛሬ ፖለቲካን አክ እንትፍ ብለው
ሌላ ስልጣኔ ጆሊነት ጀምረው
ቆዳ ሱሪ ለብሰው
በሬጌ ሙዚቃ በግራዋ ሰክረው
እዛው ባህር ማዶ ፈረንጅ ሀገር ናቸው።

እነ እንትና ደግሞ ጧት ጧት ይሰራሉ
ማታ ይጠጣሉ
ወይ እንደነ እንትና ገንዘብ አጠራቅመው
በሀብት አልከበሩ
ወይ እንደነ እንትና ት/ቤት ገብተው
ትምህርት አልተማሩ
ወይ እንደነ እንትና ጆሊነት ጀምረው
ሬጌ አልዘፈኑ
በመጠጥ ብዛት ተጠብሶ ፊታቸው
አምቢ ተቀብተው መስሎ የላጣቸው
ቶሎ እየተቆጡ ሰው ሲያናግራቸው
እዛው ባህር ማዶ ፈረንጅ ሀገር ናቸው።

እነ እንትና ደግሞ ፖለቲካ ሳይንስ፤ ኢኮኖሚ አጥንተው
ትልቅ ቦታ ይዘው ፕሮፌሰር ተብለው
በየስብሰባው ላይ ተጠሪዎች ሆነው
ተወካዮች ሆነው
ለኢትዮጵያ ጠቃሚው
ሊበራሊዝምና ነጻ ገበያ ነው
ንግድ ቢስፋፋ ነው
ማለት ቢጀምሩም
እንዴት  እንደሚሆን መንገድ አላሳዩም
ለወሬ የሚመች ሰፊ ሀገር ነው ብለው
እዛው ባህር ማዶ ፈረንጅ ሀገር ናቸው።

እነ እንትና ደግሞ ዛሬም እንደድሮው
ለዕውነት ለመስራት መፍትሄ ለማግኘት
ከልብ ቢጥሩም
ሰውን ማደራጀት መቀስቀስ ከብዷቸው
እዛው ባህር ማዶ ፈረንጅ ሀገር ናቸው።
እነ እንትና ደግሞ ዛሬም ትምህርት ቤት
ከኮሌጅ ቢሆኑም


መማር ማመራመር ምሳሌ ቢሆኑም
ለመቼ እንደሆነ በደንብ አልገባንም።
ስራ ባይጀምሩም አንድ ቀን ጨርሰው
ጡረታው ከፍ ይላል የሚል ወሬ ሰምተው
እዛው ት/ቤት ፈረንጅ ሀገር ናቸው።

እነ እንትና ደግሞ እኩልነት ትተው፤
በአቋራጭ ለመክበር ለመኖር ወስነው
ቀለም ተቀባብተው በጌጣጌጥ ደምቀው
እዛው ባህር ማዶ ፈረንጅ ሀገር ናቸው።
እነ እንትና ደግሞ ሦስት መቶ ስድሳ ቀን ሥራ ይሰራሉ፤
ጳጉሜ ጳጉሜ ሲደርስ እየተገናኙ ኳስ ይጫወታሉ፤
የኢትዮጵያ ቡድን ድሮ የምናውቃቸው
እዛው አሜሪካ ባህር ማዶ ናቸው።

እነ እንትና ደግሞ ለስራ ተልከው፤
ሥልጣን በቃን ብለው አሳይለም ጠይቀው፤
እጃቸውን ታጥበው ንጹህ ሰዎች ሆነው፤
መጻሕፍት ደርሰው፤ በቲቪ ተናግረው፤
ለቃለ መጠይቅ በሬዲዮ ቀርበው፤
ታሪክ አዋቂዎች ምስክሮች ሆነው፤
ዛሬ እንደ ድሮው ነግደው አትርፈው፤
እነሱ ተናግረው እኛን ሰሚ አድርገው፤
እዛው ባህር ማዶ ፈረንጅ ሀገር ናቸው።

እነ እንትና ደግሞ፤ እነ እንትና ደግሞ፤ እነ እንትና ደግሞ
ብዬ ያየሁትን እውነቱን ልንገረው?
ወይስ እንዳያዝን፤ ይበልጥ እንዳይከፋው
እውነቱን ሸሽጌ፤ በውሸት ሸፍኜው፤
እንደው በደፈናው ሁሉም ደህና ናቸው፤
ያለፈውን ውድቀት ስህተቱን ተረድተው
ለማረም ወስነው፤
ባንድ ድርጅት ሥር ባንድ አመለካከት
ላንድ ዓላማ ቆመው፤
የተሻለ ነገር ሊወስዱ አገራቸው፤
እየተዘጋጁ እያሰቡበት ነው፤
ብዬ ላስደስተው?
ያንን አብሮ አደጌን ያንን ጓደኛዬን
ቀን ያለያየንን፤
ደግሞ ቀን ወጥቶልን፤
ቀን ለእኛ ሆኖልን
አንድ ቀን ባገኘው፤
ሳስበው ጨነቀኝ
እስቲ መላ ስጡኝ
ምን ብዬ ልንገረው?

ደራሲው ያልታወቀ (Anonymous)



'ዓለም በቃኝ' በመባል ይታወቅ የነበረውና በአስራ ሰባቱ የደርግ ወታደራዊ አገዛዝ ወቅት በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የተሰቃዩበት እስር ቤት

# ከዚህም ከዚያም

## የኮሪያ ማስታወሻ

እ. ኤ. አ. ያለፈውን ዓመት (2014) ጥቅምት ወር በሙሉ ያሳለፍኩት በሥራ ምክንያት ኮሪያ ነበር። በዚያ ዓመት ኮሪያ ስገኝ ሁለተኛዬ መሆኑ ነበር። በመጀመሪያ ዙር ጉዞዬ የኮሪያ ዋና ከተማ ሶል (Seoul) ውስጥ የሚገኘውን የኮሪያ ጦርነት መታሰቢያ ሙዚየምን ጎብኝቼ ነበር። በኮሪያ ጦርነት ለተሳተፉ ኢተዮጵያውያን በተለየ የተዘጋጀ መታሰቢያ ቹንቾን (Chuncheon) በሚባል ከተማ እንደሚገኝ ኮሪያዊያን ጓደኞቼ ነግረውኝ ስለነበር በጥቅምቱ ጉዞዬ መታሰቢያውን ለመጎብኘት ተዘጋጅቼ ነበር የሄድኩት።

የጥቅምቱ የኮሪያ ቆይታዬ ፒዮንግቻንግ (Pyeongchang) በሚባል በአገሪቱ ሰሜን ምሥራቅ በጋንጋዋን ክፍለ ሃገር በሚገኝ ከተማና አካባቢው ነበር። ፒዮንግቻንግ እ. ኤ. አ. በ2018 የክረምት ኦሎምፒክን ለማስተናገድ በዝግጅት ላይ የምትገኝ ከተማ ናት። ቹንቾን ደግሞ ከፒዮንግቻንግ በመኪና ከሁለት ሰዓት በላይ በሚወስድ ርቀት ላይ ነው የምትገኘው።

ከጥቂት ቀናት የፒዮንግቻንግ ቆይታዬ በኋላ ቅዳሜ ኦክቶበር 4 ቀን 2014 ወደ ቹንቾን ለመሄድና ለኢትዮጵያውያን የኮሪያ ዘማቾች የተሠራውን መታሰቢያ ለመጎብኘት ወሰንሁ። ፒዮንግቻንግ ውስጥ የነበረኝ ተልዕኮ በተባበሩት መንግሥታት ከተዘጋጁ ትላልቅ ኮንፈረንሶች ጋር የተያያዘ ነበር። የኮንፈረንሱን ጸጥታና የተሳታፊዎችን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ከተለያዩ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መሥሪያ ቤት ከሚገኝባቸው የዓለም ከተሞች የተውጣጡ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጸጥታና የደህንነት አባላት በአካባቢው ተሠማርተው ነበር። ከነዚህ አባላት ውስጥ አዲስ አበባ ከሚገኘው የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የመጡ ስድስት ኢትዮጵያውያን ነበሩ።

ወደ ቹንቾን ለመሄድ ስዘጋጅ ስድስቱ ኢትዮጵያውያንም አብረውኝ ይሄዱ ዘንድ አማከርኳቸው። በሃሳቡ ተስማሙ። ከሥራቸው የአንድ ቀን ፈቃድ ያገኙ ዘንድ ኃላፊያቸውን አነጋገርኩ። በኮሪያው ጦርነት የኢትዮጵያ ሠራዊት አባላት የተሳተፉት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሥር ስለነበር የስድስቱ




ኢትዮጵያውያን መታሰቢያውን መጎብኘት ታሪካዊነቱን ጠቃቅሼ አለቃቸው ፈቃድ እንዲሰጣቸው በጠየቅሁት መሠረት ስምምነቱን ገለጸልኝ። መኪናም ተከራየሁ። ኦክቶበር 4 ቀን 2014 አንድ የኮሪያ ሠፈር ልጅ (እኔ) እና ስድስት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጸጥታና ደህንነት አባላት (አድማሱ ወሮሳ፣ ባህሩ መሐመድ፣ ዳንኤል ታምራት፣ ሸዋዬ አንተነህ፣ ጽጌረዳ፣ እና ተስፋዬ ወርቁ) በጥዋት ተገናኝተን ጉዟችንን ወደ ቹንቾን ጀመርን።

ከሁለት ሰዓት ጉዞ በኋላ ቹንቾን ከተማ ገባን። የአብዛኛው ሕንጻዎች ቀለም ደብዛዛ ነጭ ሲሆን መንገዶችም በአግባቡ የተያዙና የኮሪያ ኢንዱስትሪ ውጤት የሆኑ ምርቶችን፣ ሳምሰንግን ጨምሮ፣ የሚያስተዋወቁ ስሌዳዎች በየቦታው የሚታዩበት ከተማ ነው። ከኮሪያዊው የመኪናችን አሽከርካሪ ጋር ለመግባባት ቋንቋ ቢያስቸግረንም፣ የት እንደሚወስደን ከመነሻችን በአስተርጓሚ ተነጋግረን ስለነበር፤ በቀጥታ በኢትዮጵያ ስም ወደ ተሰየመ አንድ አጭር መንገድ ይዞን ገባ። ወዲያውኑ እኛም የአገራችን ሰንደቅ ዓላማ ሲውለበለብ አየን። ጠጋ ስንልም “የኢትዮጵያ ቤት” የሚል በአማርኛ በጉልህ የተጻፈበት ሕንጻ አየን፤ ከሕንጻው ፊት ለፊትም የቡና ፍሬ ቅርጽ ወይም የደቡብ ኢትዮጵያ የገጠር ቤቶችን የመሰሉ የተያያዙ ሦሥት አነስተኛ ሕንጻዎች ተመለከትን። በሕንጻዎቹ ግንባር ላይ “Memorial Hall for Ethiopian Veterans in the Korean War” የሚል በእንግሊዝኛና በኮሪያ ፊደላት በጉልህ የተቀረጸውን አነበብን። ከጽሁፋም በላይ በኮሪያ ጦርነት ተዋጊዎች ወይም የሕክምና ባለሙያዎች በመላክ በተባበሩት መንግሥታት ስም ከደቡብ ኮሪያ ጎን የቆሙት የአስራ ስድስት አገሮች ባንዲራዎች ይውለበለባሉ። በአረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለማት የተዋበውን የአገራችንን ባንዲራ ስንመለከት ሁላችንም በከፍተኛ ስሜት ውስጥ ገባን።




ወደ መታሰቢያ አዳራሹ እንደገባን ኮሪያዊቷ አስተናጋጅ ኢትዮጵያዊነታችንን በመለየት ወዲያውኑ ስለ ኢትዮጵያዊያን የኮሪያ ጦርነት ተሳትፎ፤ ስለ ቃኘው ጦር የውጊያ ገድል የሚያትት፣ የድምጽ መግለጫው በአማርኛ የተዘጋጀ የቪዲዮ ፊልም እንድንመለከት ጋበዘችን። ፊልሙ የሚመስጥ ነበር። በአንድ በኩል ኢትዮጵያዊ ኩራትን የሚያላብስ በሌላ በኩል ግን በጦርነቱ ወቅት በዕድገታቸው የጎላ ልዩነት ያልነበራቸውን ኢትዮጵያንና ኮሪያን (ደቡብ ኮሪያን) በማወዳደር አሁን ኮሪያ የደረሰችበትንና ኢትዮጵያ ያለችበትን ሲያስቡት የቁጭት ስሜትን የሚፈጥር ነበር።

በፊልሙ ውስጥ ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የኮሪያ ዘማቾች ኢትዮጵያዊን መካከል አንድ ሁለቱን በመልክ የማውቃቸው ነበሩ። ፊልሙ በትዝታ ሁላችንን የማረከ ሲሆን በተለይ ተስፋዬ ወርቁ አባቱ የኮሪያ ዘማች ስለነበሩ አንዳንድ ጊዜ በስሜት ብዛት የፊልሙ ማሳያ ሰሌዳ ላይ እየተወረወረ አስቸገሮን ነበር። እኔም በበኩሌ ሰውነቴን የሚነዝሩ ትዝታዎች ተቀስቅሰውብኝ ነበር። የቀድሞ የኮሪያ ዘማች የነበሩና በድህነት የተነሳ ጭቃ በማቡካትና ቤት በመለሰን ይተዳደሩ የነበሩት አቶ መኩሪያ የሚባሉ የሠፈራችንን ነዋሪ አስታወስኩ።

የኢትዮጵያው ቃኘው ጦር እ. ኤ. አ. ከ1951 እስከ 1954 በተካሄደው የሁለቱ ኮሪያዎች ጦርነት በደቡብ ኮሪያ በኩል ተሳትፏል። በተለያዩ ዙሮች በጠቅላላው 6035 ኢትዮጵያውያን ወታደሮች የተሳተፉ ሲሆን፤ ጦሩ 253 የተለያዩ ውጊያዎች አድርጎ 121 አባላቱ ሲሰዉ፣ 536 ያህሉ ደግሞ የተለያየ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። አንድም ኢትዮጵያዊ ወታደር በምርኮ አልተወሰደም። ጦሩ በውጊያ የተሰማራባቸው ቀጠናዎች ቱንቾን፣ ህዋቾን፣ ቾሎን፣ ያንጉ እና ጋፒዮንግ ይባላሉ።

የኢትዮጵያውያን የኮሪያ ጦርነት ዘማቾች መታሠቢያ የተሠራው እ.ኤ.አ. በ1968 ዓ.ም. ነበር። የመታሰቢያ አዳራሹ የተለያዩ ኢትዮጵያን የሚያስተዋውቁ ፎቶዎች፣ ቅርሳ ቅርሶችና የጽሑፍ መረጃዎችን የያዘ ሲሆን በጦርነቱ ሰማዕታት የሆኑት የ 121 ኢትዮጵያውያን ስሞችም በአንድ ግድግዳ ላይ በተለጠፈ ሰሌዳ ላይ በወርቅማ ቅብ ተዘርዝረዋል።

ከመታሰቢያ አዳራሹ ውጪ የተለያዩ ቤቶችና ኪዮስኮች ያሉ ሲሆን ኢትዮጵያን የሚያስተዋውቁ ጽሑፎችና ምስሎች ይታይባቸዋል።

በአንድ "የኢትዮጵያ ቤት" የሚል በጉልህ በተጻፈበትና የኢትዮጵያን ባንዲራ የተሸከመ አንበሳ ምስል በሚታይበት ሕንጻ ውስጥ ስንገባ በኮሪያውያን ተሞልቶ አገኘነው። ውስጡ በኢትዮጵያ ባንዲራና በቡና ሽታ ታውዷል። ኮሪያውያኑ ቡና እየጠጡ ነበር። አስተናጋጆቹ ከኢትዮጵያ የተለያዩ የቡና አብቃይ አካባቢዎችን ስም እየጠሩ ቡና ያስተዋውቃሉ፤ እዚህም እዚያ የቡና ቅምሻ ተጧጡፏል። እኛም የይርጋ ጨፌ ይሻላል፣ ወይስ የሐረር እያልን አማርጠን የተወሰነ ቀማምሰን ወጣን።

ከዚያም ከአዳራሾቹ በ100 ሜትር ያህል ርቀት ላይ የሚታየውን ለኢትዮጵያውያኑ መታሰቢያ ተብሎ የቆመውን ሃውልት ጎበኘን። ለምሳችንም መንገድ ዳር ተዘጋጅተው ከሚሸጡት ቅንጥብጣቢዎች በላላን። በመንገድ ዳር ሙዚቃ ተዝናናን፣ አንዳንድ ኮሪያውያንንም መግባባት እስከቻልን ድረስ አውርተን ወደ አመሻሹ ላይ በተከራየነው መኪና ጉዞአችንን ወደ ፒዮንግቻንግ አደረግን። በዚያ ታሪካዊ ጉዞአችን ያየነውን ለዘመድ ለጓደኛ ለማካፈልም የተወሰነዉን በፎቶግራፎችና በቪዲዮ ፊልሞች ቀርጸን ተመለስን።

ወርቁ ዳመና
እ. ኤ. አ. ኦክቶበር 18 ቀን 2014
ፒዮንግቻንግ፤ የኮሪያ ሪፓብሊክ

# የኮሪያ ዘማቿ ማህደር



ምክትል የመቶ አለቃ ሲስተር ብርቅነሽ፣ ኮሪያ ከዘመቱት ሁለት ሴት ነርሶች አንዷ ናቸው፣

ተወልደው ያደጉት አዲስ አበባ ከተማ ነው፤ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ግርማዊት እቴጌ መነን ትምህርት ቤት ገብተው ተምረዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀይ መስቀል ነርስ ትምህርት ቤት ሲቋቋም ለመግባት ከተፈተኑት 11 ወጣቶች አንዷ ነበሩ። ከተፈተኑት መካከል እሳቸውን ጨምሮ ዘጠኙ አለፉና የመጀመሪያው የቀይ መስቀል ነርሲንግ ትምህርት ቤት ተማሪ ሆኑ። በዚህም ትምህርት ቤት ለሦስት ዓመት የነርሲንግ ትምህርት እንዲሁም ለስድስት ወራት የማሳጅ ኮርስ ከተከታተሉ በኋላ በኢትዮጵያ ከመጀመሪያዎቹ ሴት ነርሶች መካከል አንዷ በመሆን ለመመረቅ በቅተዋል።

ምክትል የመቶ አለቃ ሲስተር ብርቅነሽ ከበደ ከሦስተኛው ቃኘው ሻለቃ ጋር ኮሪያ ከዘመቱት ሁለት ሴት ነርሶች አንዷ ናቸው። እንደ ምክትል መቶ አለቃዋ አባባል፣ የመጀመሪያው ዙር የቃኘው ሻለቃ ጦር ከኮሪያ ዘመቻ በኋላ ወደ እናት አገሩ ሲመለስ በዘመቻው ወቅት ኢትዮጵያውያን ሐኪሞችና አስተርጓሚዎች ባለመኖራቸው የተነሳ ችግር ተፈጥሮ እንደነበር ለበላይ አካል ያሳውቃሉ። ይህም ጉዳይ የግርማዊት እቴጌ መነን ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህርና የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር የቦርድ አባል ለነበሩት ወ/ሮ ስንዱ ገብሩ ዘንድ ደርሰ። ወ/ሮ ስንዱም ጉዳዩን ለግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ አቀረቡ። ንጉሠ ነገሥቱም ከቀይ መስቀል ማኅበር ነርስ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ተመራቂዎች መካከል ፈቃደኛ የሆኑ እንዲዘምቱ ንጉሣዊ ትዕዛዝ ሰጡ። በዚህም መሠረት እሳቸውና ሲስተር አስቴር አያና ፈቃደኞች ሆነው ተገኙ።

ከተመረቁም ከሁለት ወራት በኋላ መሠረታዊ የሆኑ ወታደራዊ ሥልጠና (ሰላምታ አሰጣጥ፣ ተኩስ ወዘተ) ሠልጥነው እንዳበቁ ለእያንዳንዳቸው የምክትል መቶ አለቅነት ማዕረግ ተሰጥቷቸው ከሦስተኛው ቃኘው ሻለቃ ጦር ጋር ተሰልፈው ዓለም አቀፍ ግዳጃቸውን ለመወጣት በ1945 ዓ.ም. ወደ ኮርያ አቀኑ። ከአዲስ አበባ እስከ ጂቡቲ በባቡር ከዛም በመርከብ ተጓዙ። ኮሪያ ለመድረስ 21 ቀንና ሌሊት እንደፈጀባቸው ነው ምክትል የመቶ አለቃ ሲስተር ብርቅነሽ የተናገሩት።

ይህም ሆኖ ግን በጉዞአቸው ላይ የመሰላቸት ነገር አላጋጠማቸውም። ምክንያቱም መርከቡ ላይ ሁልጊዜ ማታ ማታ ልዩ ልዩ ዓይነት የመደሰቻ፣ የመዝናኛና የሙዚቃ ፕሮግራሞች ነበሩ። ደረጃቸውን በሚገባ የጠበቁ ሱቆችም ስለነበሩ የፈለጉትን የመሸመት ዕድል እንደነበራቸው ይናገራሉ። ወጣትነታቸው ደግሞ ነገሮችን እንደአመጣጣቸው እንዲቀበሉ ረድቷቸዋል።

ምክትል መቶ አለቃ ሲስተር ብርቅነሽ ወደ ኮሪያ የዘመቱት የ21 ዓመት ወጣት ሳሉ ነው። የሕክምና አገልግሎት መስጠት የጀመሩትም ገና በመርከብ ጉዞ ላይ እንዳሉ ነበር። ብዙዎቹ ወታደሮች ሲ-ሲክነስ (የባህር ጉዞ ላይ በሽታ) ታመው ያቅለሸልሻቸውና ያስመልሳቸው ነበር። የመርከቡ ሐኪም፣ ነርሶች መሆናቸውን ሲያውቁ በመርከቡ ምድር ቤት ውስጥ በተቋቋመው ክሊኒክ ውስጥ ሆነው አገልግሎት እንዲሰጡ አደረገ። በዚህ መልክ ተገቢውን ዕርዳታ እየሰጡ በመጓዝ በመጨረሻ ኮሪያ ሉሳን ከተማ ገቡ። በዚህም ለ25 ቀን ያህል ቁስለኞችን ሲያክሙ ከቆዩ በኋላ መደበኛ ሥራቸውን ለመጀመር ወደ ጃፓን ቶኪዮ እንዳቀኑ አጫውተውናል።

ኮሪያ ላይ ለቁስለኞቹ የሚደረግላቸው የመጀመርያ ሕክምና ዕርዳታ ነው። ከአቅም በላይ የሆነውን ሕክምናቸውን የሚከታተሉት ግን ቶኪዮ ጃፓን ውስጥ በሚገኙትና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ባቋቋማቸው ሦስት ሆስፒታሎች ውስጥ ነው። ከእነዚህም ሆስፒታሎች ውስጥ ሁለቱ <<አኔክስና ሜን>> ሆስፒታሎች ሲባሉ አንደኛው ደግሞ <<ኤይት ዋን>> የሚባል የአዕምሮ ሕሙማን ሆስፒታል ነው። ምክትል የመቶ አለቃ ሲስተር አስቴር፣ ሜን ሆስፒታል፣ ምክትል የመቶ አለቃ ሲስተር ብርቅነሽ ደግሞ አኔክስ ሆስፒታል ተመድበው ግዳጃቸውን መወጣት ተያያዙት።

በእነዚህ ሆስፒታሎች የሕክምና አገልግሎት የሰጡት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስር ዘምተው ለቆሰሉ ኢትዮጵያን ጨምሮ ለሁሉም አገሮች ወታደሮች ነው። ከሕክምና ሥራቸው ባሻገር ሌላ በተጨማሪ ለኢትዮጵያ ወታደሮች የማስተርጎም ሥራ ያከናውኑ እንደነበር ነው ምክትል የመቶ አለቃ ሲስተር ብርቅነሽ የሚናገሩት። በተመደቡበት አኔክስ ሆስፒታል እየቆሰሉ ከሚመጡት መካከል፣ በተለይ የኢትዮጵያ ቁስለኛ ወታደሮች በሕክምና እያሉና ገና ሳያገግሙ <<የጠቅል አሽከር!>> እያሉ በመፎከር እንደገና ወደ ጦር ግንባር መልሱን እያሉ ያስጨንቁና ይጠይቁ ነበር። የሌሎች አገሮች ቁስለኛ ወታደሮችም የኢትዮጵያን ቁስለኛ ወታደሮች ወኔና ጀግንነት በማየት በጣም ይደነቁ ነበር። የሌሎቹ አገር ቁስለኞች በሽታቸውን ማስታመም እንጂ፣ መልሱን የሚል ጥያቄ እንደማያቀርቡ፣ ቁራሹንም እንደማያስቡት ገልጸዋል።

በዘመቻው ላይ ምግባቸው ከአሜሪካ በጣሳ ታሽጎ ይመጣላቸው እንደነበርና በዚህ በኩል የገጠመ ችግር እንደሌለ ገልጸዋል። ነገር ግን ወደ ኮርያ በመርከብ በመጓዝ ላይ እንዳሉ፣ የፋሲካ በዓል እንደደረሰ፣ በዚህም የተነሳ የባህር ምግብ ሽሪምፕ እንደቀረበላቸው እሳቸውና ሌሎቹ መኰንኖች የቀረበላቸውን ሲመገቡ ወታደሮቹ ግን <ይኼን ምግብ አንበላም> በማለት እንደተጠየፉትና በምትኩ ዳቦ በልተው እንደዋሉ በዚህም አስተናግጆች በጣም እንደተደናገጡ ነግረውናል።

ምርከኞችን በተለከተም <<የተማረከ ወታደር ሁሉ ሲመጣ ወይም የምርከኞች ልውውጥ በሚደረግበት ጊዜ እኔና ምክትል የመቶ አለቃ ሲስተር አስቴር ተኝተን እንውል ነበር። ምክንያቱም አንድም የተማረከ የኢትዮጵያ ወታደር ስለሌለ ነው>> ይላሉ።

ያገለግሉበት በነበረው ሆስፒታል ውስጥ ልብሶቻቸውን የሚያጥቡላቸው ጃፓኖች ነበሩ። በተለይ ትከሻቸው ላይ የሚያንጠላጥሉት የኮከብ ማዕረግ ክብር ያሰጣቸው ነበር። በአንድ ወቅት የታጠበላቸውን ልብስ ለማምጣት ሲሄዱ አንድ የኮሪያ ወታደር በተጠንቀቅ ቀጥ ብሎ ቆመና ሰላምታ ሰጣቸው። እሳቸውም ዝም ብለው ሰላምታ ሰጥተውት አለፉ። ወታደሩ ይሄንን ያደረገው የምክትል መቶ አለቅነት ማዕረግ የሆነውን ኮከብ አይቶ <<ዋን ስታር ጄኔራል>> ወይም ባለ አንድ ኮከብ ጄኔራል መስለውት እንደነበር ያስታውሳሉ። በእነሱ አገር አንድ ኮከብ የጫነ መኰንን ዋን ስታር ጄኔራል ሲሆን፣ በእኛ አገር ደግሞ የምክትል መቶ አለቃ ማዕረግ ነው።

በዘመቻ ቆይታቸውም የአሜሪካ ሙዚቀኞች በየተራ እየመጡ ያዝናኗቸው እንደነበር፣ በተለይም በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየችው ማርሊን ሞንሮ <<ከነጭፍሮቿ>> እየመጣች በይበልጥ ታዝናናቸው እንደነበር ከምክትል መቶ አለቃ ሲስተር ብርቅነሽ ይገልጻሉ።

የኮሪያ መንግሥት ላበረከቱት አስተዋጽኦ ለምክትል መቶ አለቃ ሲስተር ብርቅነሽ ከፍተኛ ድጋፎችን አድርጎላቸዋል። ከተደረገላቸውም ድጋፎች መካከል ኮሪያን እንዲጎበኙ መጋበዛቸውንና በራሳቸው ምክንያት ግን ለመሄድ እንዳልቻሉም፣ አዲስ አበባ በሚገኘው ኮሪያ ሆስፒታል ነፃ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ መደረጉንና በየወሩም 700 ብር በጡረታ አበል መልክ እየከፈላቸው መሆኑን ነው።

ከዚህም ሌላ በድምሩ አምስት ደረት ላይ የሚለጠፍ ኒሻኖች ተሸላሚ ሆነዋል። ከእነዚህም መካከል ከኢትዮጵያ መንግሥት የንግሥት ሳባ የክብር ኮከብን ጨምሮ ሦስት ልዩ ልዩ ኒሻኖች፣ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አንድ ኒሻንና ጄኔቭ ከሚገኘው የዓለም ቀይ መስቀል ማኅበር የፍሎሬንስ ናይትንጌል ኒሻን ይገኙባቸዋል። <<ከተበረከቱልኝ ኒሻኖች ሁሉ በይበልጥ ደስ የሚለኝ የፍሎሬንስ ናይትንጌል የኒሻን ሽልማት ብቻ ነው። ምክንያቱም ይህን ኒሻን ያገኘሁት ዘምቼ የጦር ቁስለኞችን በማከም ዓለም አቀፍ ግዴታዬን በመወጣቴ ብቻ ሳይሆን ከጄኔቭ የተላከልንን ሰብዓዊ አገልግሎቶች የተመለከተ ፈተና በጥሩ ሁኔታ በማለፌም ጭምር ነው። ፈተናውም የታረመው ወደ ጄኔቭ ተወስዶ ነው፤>> ይላሉ።

ግዳጃቸውን ፈጽመው ወደ አገራቸው እንደተመለሱ የመጀመሪያው የኮሪያ ዘማች ከነበሩትና አሁንም በሕይወት ካሉት ብርጋዴር ጄኔራል ደስታ ገመዳ ጋር በሕግ ተጋብተው ትዳር መሠረቱ። ትዳር ከመመሥረታቸው በፊት ፍቅረኛሞች እንደነበሩ፣ የውትድርና ሙያና አንድ መኰንን በግዳጅ አፈጻጸም ወቅት ማከናወን በሚገባው ተግባር ላይ ትኩረት ያደረገውን ሥልጠና

እንዲሰጧቸው የተመደቡት፣ በጊዜው የክብር ዘበኛ ሆስፒታል አስተዳዳሪ ሆነው የሠሩትና ፍቅረኛቸው የነበሩ የአሁኑ ባለቤታቸው ናቸው። ባልና ሚስቱ በአሁኑ ወቅት ከአብራካቸውም የተገኙ ሦስት ወንዶችና አንድ ሴት ልጆች አሏቸው። የልጅ ልጅ ለማየትም በቅተዋል። ከባለቤታቸው ጋር በጋብቻ ከተሳሰሩ የፊታችን ሚያዝያ 60 ዓመት ይሆናቸዋል።

በክብር ዘበኛ ሆስፒታል ውስጥ ለአራት ዓመታት ያህል እንዳገለገሉ፣ ከዛም የካቲት 12 ሆስፒታል በምክትል ሜትረንነት፣በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል በሙሉ ሜትረንነት፣ ካዛንቺስ በሚገኘው በቀድሞው አባላዘር መከላከያ (ቦርቾሌ) የጤና ተቋም፣ እንዲሁም ቂርቆስ የእናቶችና ሕፃናት ክሊኒክ በአጠቃላይ ለ47 ዓመታት ያህል ካገለገሉ በኋላ በ1984 ዓ.ም. በክብር በጡረታ ወጥተዋል።

የኢትዮጵያ ነርሶች ማኅበር አባል ነዎትን? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ምክትል የመቶ አለቃ ሲስተር ብርቅነሽ <<አይደለሁም፣ አልተጋበዝኩም፣ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን እኔ በማኅበሩ አልፈርድም። ምክንያቱም አንደኛ እኛ የመጀመሪያዎቹ ነርሶች ራሳችንን አላስተዋወቅንም። ማኅበሩንም አልተጠጋነውም። ከመጀመሪያዎቹ የቀይ መስቀል ነርሶች መካከል በሕይወት ያለነው እኔና አንዲት ሌላ ነች። በተረፈ የቀሩት ሁሉ አልቀዋል ሞተዋል)>> ሲሉ መልሰዋል።

ተጻፈ በ ታደሰ ገብረማርያም
ምሕረት ሞገስም አስተዋጽኦ አድርጋለች
12 November 2014 - ኅዳር 3, 2007 ዓ.ም.
ታትሞ ከወጣው ሳምንታዊው የሪፖርተር ጋዜጣ
የማህበራዊ ዓምድ የተወሰደ
http://www.ethiopianreporter.com/index.php/other-sections/social-affairs/social/item/7841-የኮሪያ-ዘማቹ-ማህደር



# የቀበና ትዝታ

## ቀበና ከግማሽ ምዕተ ዓመት በፊት

በእዚህ ጽሁፍ ላካፍላችሁ ያሰብሁት የቀበናን የልጅነት ትውስታዬን ነው። የቀበና እና የአካባቢው መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ እንዴት ነው? የወንዙ ምንጭ መነሻና መድረሻ የት ነው? የህዝቡ የመጀመሪያ አሰፋፈር ምን ይመስል ነበር? የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ እሞክራለሁ። ይህንን መጠነኛ ጆኦግራፊያዊና ማህበራዊ ታሪክ አሁን ላለውም ሆነ ለተተኪው ትውልድ ማሳወቅ መልካም ነው ብዬ አምናለሁ።

### የቀበና ወንዝ

እንደምታውቁት "ቀበና" ወንዝ ነው። ቀበና የፈሳሹ የወንዙ ስም ቢሆንም አጎራባች የሆኑት ሰፈሮች ሁሉ ስሙን ይጠቀሙበታል። ወንዙ ከእንጦጦ አካባቢ ተነስቶ፣ "ሰባት መጫኛ" የሚባለውን ባሕር አቋርጦ፣ በእቴጌ መስክና በአሜሪካን ኤምባሲ ጀርባ አድርጐ በፈረንሳይ ለጋሲዮን አጠገብ አልፎ፣ ኮንጐ ሠፈርን፣ ጋራ ጓላን፣ ሽክላ ሜዳን፣ ትግሬ ሜዳን፣ ኮሪያ ሠፈርን አቋርጦ ዱቤ ባሕር ይገባል። ሌላው ደግሞ የአቦ ጅረት ሲሆን መነሻው ከአሞራ ገደል አጠገብ ሲሆን፣ የጥንስስ ባሕርን አቋርጦ፣ በዳንሴ ጋራ ጥግ ጥግ አዋስኖ፣ በጣልያን ኤምባሲ ጀርባ አልፎ፣ "መነፅር" የምንላትን መዋኛ ባሕር አልፎ፤ ዱቤ ባሕር ላይ ከቀበና ወንዝ ጋር ይቀላቀላል። ሁለቱ ወንዞች የሚፈጥሩት ወንዝ የቀበናን ስም ይይዝና የብረት ድልድይንና የቀ.ኃ.ሥ ድልድይን አልፎ፣ በአስፋው ወሰን መለስተኛ አጠቃላይ ት/ቤት አድርጎ፣ ቀድሞ የኢትዮጵያ የሙብራት ኃይል ማመንጫ ከነበረው "አባ ሣሙኤል" ከሚባለው ሐይቅ ይገባል።

የቀበና ውሃ ንጽህናው ኩል ይመስል ስለነበረ በውስጡ የሚንቀሳቀሱትን እንቁራሪቶችም ሆኑ ዓሣዎች ለማየት አያስቸግርም ነበር። በተጨማሪ ከሩቅ ቦታ የሚመጡ ሰዎች ወይም ተላላፊዎች እንዲሁም የክብር ዘበኛ ወታደሮች ከጦር ልምምድ በኋላ ገላቸውን የሚታጠቡበት ወንዝ ነበር። ብዙ ሰዎች ልብሳቸውን የሚያጥቡትም ሆነ ገላቸውን የሚታጠቡት በቀበና ወንዝ እንደነበር አስታውሳለሁ። ከፒያሳም ሆነ ከመርካቶ ከአራት ኪሎም ሆነ ስድስት ኪሎ፣ ወጣቱ ሁሉ እየጐረፈ መጥቶ የሚዋኝበት መልካም የመዝናኛ ቦታም እንደነበረ አይዘነጋኝም። በተጨማሪም አጋምና ቀጋ እንዲሁም ኮሽም የሚለቀምበት ቦታ ነበር። የቀበናም ሆነ የአቦ ወንዝ ከዓመት እስከ ዓመት ሳይደርቁ የሚፈሱ ወንዞች ነበሩ። ውሃው ዓመቱን በሙሉ ስለሚፈስ ከብቶች የሚግጡት ሣር፣ የሚጠጡት ውሃ እንደልብ ነበር። በኋላ ግን ግለ ሰቦችም ሆኑ ኤምባሲዎች ለግል ጥቅማቸው ወደ ግቢያቸው የወንዙን ውሃ መጥለፍና መጠቀም ሲጀምሩ ወንዞቹ በበጋ ሰዓት እስከ መድረቅ ደርሰዋል።



## ሠፈሮች፣ ሜዳዎችና ኮረብታዎች

ቀበና በጣም ረጅም ስለሆነ ሠፈሮቹን ለመግለጽ ከመነሻው ከእንጦጦ ይዤ መውረዱን አልሞከረውም። የተወሰነውን ነው ለመቃኘት የምሞክረው። ይኸውም ኮንጎ ሠፈር፣ ጋራ - ኳላ፣ ሸክላ ሜዳ፣ ትግሬ ሜዳ፣ ኖራ ሜዳ ፣ ኮሪያ ሠፈር፣ ቤላ ሠፈር፣ ቆርቆሮ ሠፈር፣ ቅንብቢት ሠፈሮችን ይሆናል።

ከማይጨው ጦር ሠፈር ወርዶ ፈረንሳይ ለጋሲዎን መዳረሻ ላይ ከቀበና ወንዝ ግርጌ በስተቀኝ በኩል ከሚገኘው ረባዳ ቦታ ላይ ጥቅጥቅ ያለ የባሕር ዛፍ ጫካ የነበረ ሲሆን ኮንጎ ዘምተው የተመለሱት የክብር ዘበኛ ወታደሮች በቦታው እየተመሩ ከላይ እስከ ታች የቆርቆሮ ቤት ሠርተው ጥቅጥቅ ያለ መንደር ስላደረጉት የኮንጎ ሠፈር እየተባለ ይጠራ ጀመር። ከኮንጎ ሠፈር ቀጥሎ ጋራ-ኳላ የሚባለው ኮረብታ ይገኛል። ይህ ኮረብታ የቀበና ውሃ ሞልቶ ሲመጣ የምናይበት፣ ከብቶች ስንጠብቅም እንደ ማማ (tower) የምንጠቀምበት፣ በቡሄም ሆነ በማንኛውም ጊዜ የምንገናኝበትና እንደ ስምሪት ቢሮአችን የምንገለገልበት ነበር፡ ፡ ከበታች የሚገኘው የሸክላ ሜዳ ነው። የሸክላ ሜዳ ዙሪያውን በኮረብታ ወይም ጋራ-ኳላ ተብሎ በሚጠራው ቦታ የተከበበ ሲሆን በአንድ አቅጣጫ ብቻ ከቀበና ወንዝ ጋር ይዋሰናል። ጣልያን አገራችንን ወርሮ አዲስ አበባ በገባ ጊዜ ሜዳውን፤ ኮረብታውንና ወንዙን ኢኮኖሚያዊና ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸው ሆነው ስላገኛቸው በሜዳው ላይ ትልቅ የሸክላ ፋብሪካ አቋቁሞ የነበረ ቢሆንም ሳይገለገልበት ተሸንፎ ለቆ እንደሄደ ይነገራል።

ሸክላ ሜዳ ከዓመት እስከ ዓመት ሣሩ ቅጠሉ የለመለመ ከየትኛውም አቅጣጫ ሕዝብ እየጐረፈ ጃንሜዳ ከመሄድ ይልቅ ኳስ ለመጫወት የሚሰባሰብበት አመቺ ቦታ ነበር። በበጋም ሆነ በክረምት ከየሠፈሩ እረኞች እየመጡ ከብቶቻቸውን የሚያውሉበትም ነበር። ከዚያም አልፎ ከአንድም ሁለት ጊዜ ግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ በኢትዮጵያ ስካውቶች የተዘጋጀ የጃምቡሬ ትርኢት (በዓል) የተመለከቱበት ቦታ ነበር። እንዲሁም ዝነኛው የክብር ዘበኛ ወታደር ከታህሣስ ጦርነት በፊት ለኮሪያም ሆነ ለኮንጎ ዘመቻ ዝግጅት ሲያደርግ በስዊዲኖች አማካይነት በዘመናዊ የጦር ትምህርትና ቴክኒክ የሰለጠነበት ቦታ ነበር። የቦታው አቀማመጥ ለወታደራዊ ልምምድ አመቺ ነበር። በእዚሁ ሜዳ ላይ የዘመናዊ ትግልና የጨበጣ ውጊያም ያደርጉ ነበር።

ሌላው ኖራ ሜዳ ሲሆን ዙሪያውን ከአንድ ወገን በስተቀር በገደል የተከበበ ሜዳ ነበር። ማታ ከት/ቤት ስንለቀቅ የመረብ ኳስ (ቮሊቦል) ወይም በሸራ ኳስ እግር ኳስ የምንጫወትበት ቦታ ነበር። ብዙ ጊዜ የሰፈሩም ሆነ ከባቡር መንገድ (አስፋልት የሆነ የመኪና መንገድ ማለት ነው) ክብር ዘበኞች እየመጡ ቮሊቦል የሚጫወቱበት ሜዳ ነበር። መሬቱም ሆነ የገደሉ ግድግዳ ኖራ ስለነበር አዋቂዎችም ሆነ ልጆቹ ከጨዋታ በኋላ በሙሉ ልብሳቸው ኖራ ስለሚሆን ከቀበና ጅረት ተጣጥበው/ተጣጥበን ከቤታችን እንገባለን። ከኖራ ሜዳ ወረድ ብሎ ከወንዙ ባሻገር የትግሬ ሜዳ አለች። ኖራ ሜዳ ከተያዘብን ኳስም ሆነ ልዩ ልዩ የስፖርቶች ዓይነቶችን የምንጫወትባት ቦታ ነበረች። ከሜዳው በላይ ትንሽ የምንጭ ውሃ ስለነበረች ውሃ ፍለጋ አንሄድም ነበር። በተለይም የሸክላ



የኮርያ ሠፈሮቹ

ሜዳ ተቆፍሮ ዛፍ ከተተከለበት በኋላ ዋናው መገናኛችን ትግሬ ሜዳ ነበር። የትግሬ ሜዳ ትገኝ የነበረው ከወንዙ ግርጌ ሲሆን ሁልጊዜ የቀበና ውሃ በሞላ ቁጥር እስከ ምንጭዋ ድረስ የሚያጥለቀልቃት ነበረች። ጃንሆይም ሁለት ጊዜ ለጃንቡሬ ሲመጡ ወንዙ ጊዜያዊ ድልድይ ተዘርግቶበት ወደ ሸክላ ሜዳ ያለፉት በእዚችው ሜዳ ላይ ነበር። ትግሬ ሜዳ የተባለችውም የደጃዝማች ገ/ሥላሴ መሬት ስለነበረችና ዙሪያውን ያሉት ጠባቂዎች ወይም ጭሰኞች የትግራይ ተወላጆች ስለነበሩ ነው።

በዘመኑ የቀበና ማዶ ውብ የመልክዓ ምድር አቀማመጥ ነበረው። የአዲስ አበባ ኗሪም ሆነ ከውጭ የሚመጣ እንግዳ ያንን አካባቢ ሳይጐበኘው አይሄድም ነበር። ለሽርሽርም ሆነ ለመዝናኛ የሚዘወተር፤ ብዙ ጊዜ ሠርገኞችም በአካባቢው እየመጡ የሚዝናኑበትና ፎቶግራፍ የሚነሱበት ስፍራ ነበር። በጊዜው ፎቶግራፍ መነሳት ማለት ብርቅ ነበር፤ እንደ ዛሬው ካሜራ ቀርቶ ቪዲዮ ማንሻም በየሰው ኪስ ሳይገባ ማለት ነው። የባህር ዛፉ፣ የጥዱ፣ የወይራው፣ የግራሩና የሾላ ዛፉ አበቃቀል ከፈሳሹ ውሃ ከሚወጣው ድምጽ ጋር ተጣምሮ በአንድነት ሲደመጥና ሲታይ መንፈስን ያስደስት ነበር። እንዲሁም በአካባቢው ሦስት ምንጮች ነበሩ። ከክብር ዘበኛ አጥር በታች ጐን ለጐን የነበሩት ሁለት ምንጮች ስማቸው የሾላ ውሃና ክፈተው ምንጭ የሚባል ሲሆን፤ ሦስተኛዋ ደግሞ ከቀበና ወንዝ ባሻገር የትግሬ ምንጭ የምንላት ነበረች።

ከሸክላ ሜዳ ወረድ ብሎ ወንዙን ከተሻገሩ በኋላ ወደ አቦ ቤተ ክርስቲያን በሚወስደው መንገድ በስተቀኝ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ነበረ። ቦታው የአሣማ ቤት ተብሎ ይጠራ ነበር። በአካባቢው የዱር አሣማዎች ነበሩበት ብለው ከእኛ በፊት የነበሩት ኗሪዎች ሲያወሩ እሰማ ነበር። የአሣማዎቹ ጉድጓድ እንደነበረ እኔም ደርሼበታለሁ። ቀጋም ሆነ አጋም ወይም ኮሸም ለመብላት ወደ ማዶ ማለትም ዛሬ ት/ቤት የተሠራበት ቦታ የሚሄድ ሰው ሁሉ ጉድጓዶቹን ማየት ይችል ነበር። ከፍ ብሎም ልክ የቁልቁለቱ መጀመሪያው ላይ የድንጋይ ፈለጣ ሥራ ነበር። ከዋናው መንገድ ጀምሮ እስከ እኛ መንደር ድረስ የድንጋይ መፍለጫ ነበር። የድንጋይ ቤት የሚሠራና እንዲሁም የውሃ ልክ የሚገነባ አናጢም ሆነ አስገንቢ ድንጋይ አስፈልጦ በአህያ አጓጉዞ ትሬንታ ኳትሮ እስከ ቆመበት ቦታ ወስዶ ያስጭን ነበር።

ከሸክላ ሜዳ ከፍ ብሎ የሚገኘው የኮሪያ ሠፈር ነው። ይህም መንደር የኮሪያ ሠፈር የተባለበት ምክንያት የኮሪያ ጦርነት ተመላሾች ስለሰፈሩበት ነው። የክብር ዘበኛ የቃኘው ሻለቃ ምድብ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሥር ግዳጁን ለመወጣት በባቡር እስከ ጅቡቲ ከተጓዘ በኋላ በመርከብ ተሳፍሮ ኮሪያ ዘመተ። ካልተሳሳትሁ "እልም አለ ባቡሩ ወጣት ይዞ በሙሉ" ተብሎ በክራር የተዘፈነው በዚያ ጊዜ ነበር። በወቅቱም የክብር ዘበኛ የጦሩን ስልት በዘመናዊ ጦር አሰላለፍ የቃኘበትና ችሎታውንና ብቃቱን ለዓለም ያስመሰከረበት ዘመን ነበር። ወታደሮቹ ከተመለሱ በኋላ ኮሪያ በነበሩበት ጊዜ ባጠራቀሙት ገንዘብ ከባለ ርስቱ ላይ እየተመሩ ቤቶች ሠርተው ሰፈሩ። ሲቪሊያኖችም ቦታ እየተመሩ ቤት ሰርተዋል። አካባቢው ቀደም ሲል ነጋድራስ ጳውሎስ ሠፈር እየተባለ ይጠራ ነበር። ቀደም ሲል በሰፈሩ ከ10 እስከ 15 የማይበልጡ ቤቶች በቀበሌው ሲኖሩ በአጭር ጊዜ ውስጥ አካባቢው መተላለፊያ እስከሚጠፋ ድረስ በቆርቆሮ ቤት ተጥለቀለቀ። በጊዜው የውሃ ችግር ስለነበር በቧንቧ የቦኖ ውሃ ከመግባቱ በፊት ባልሳሳት የሠፈሩ ሰው የሚገለገልበት አንድ የውሃ ጉድጓድ ነበር። የባሰበት ከወንዝ ማዶ (ከት/ቤቱ ባሻገር) የደጃች ክፈተው ምንጭ ድረስ እየሄደ ይቀዳ ነበር። ክፈተው ምንጭ ይገኝ የነበረው ከቤላው የመኪና መንገድ በታች ከጀርመን ለጋሲዮን አጥር ሥር መነፅር ባሕር አለፍ ብሎ ከቁልቁለቱ ሥር ነበር።

ሌላው ደግሞ የቆርቆሮ ሠፈር ነው። ይህ ሠፈር የሚገኘው ከጃንሜዳ በታች ከዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል በላይ የቀድሞው የክብር ዘበኛ ካምፕ ወይም የክብር ዘበኛ አርኬስትራ አባላት የሚለማመዱበት ፎቅ በታች (ወይም ትግሬ ግቢ) ነበር። በቁጥር ከ9 እስከ 12 በድንጋይ የተሠሩ መደዳ ቤቶች የነበሩት ሲሆን ከቤቶቹ በስተጀርባ ጥቅጥቅ ያለ የባሕር ዛፍ ጫካ ሆኖ ወጪ ወራጁ ለመጸዳጃ የሚገለገልበት ቦታ ነበር። የክብር ዘበኛ ግቢውን አጠቃሎ ከወሰደው በኋላ ዙሪያውን በግንብ አሳጥሮ ለኗሪዎቹም ካሳ ከፍሎ ሲያስለቅቃቸው ሁሉም ቦታውን ከደጃች ተሰማ ገድሌ እየተመሩ ከሆስፒታሉ ጀምረው እስከ ሾላው ድረስ በቤት አጥለቀለቁት። ከእነ አቶ ለገሠ ቤት ጀርባ በአቶ አረሩ ቤት በራፍ ላይ አልፎ አቶ ሣላ ከሚባሉ የጥንት ኗሪ ቤት ፊት ለፊት ከሚገኘው ሰፊ ሜዳ ላይ ማታ ማታ ከአንደኛ ፖሊስ ጣቢያ እሥረኞች በፖሊስ ታጅበው እየመጡ የሚፀዳዱበት ቦታ እንደነበረም አስታውሳለሁ።

ከዚያም አካባቢ ወረድ ብሎ የሐኪም ሜዳ ይገኛል። ሐኪም ሜዳ የተባለው ምናልባት የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ከሜዳው በላይ ስለነበረ ይሆናል። የሆስፒታሉ ልብስ አጣቢዎችና ምግብ አብሳዮች ወደ ሜዳው የሚወጡባትና የሚገቡባት በርም ነበረች። ልብስ የሚያጥቡትም ዱቤ ባሕር ነበር። ከባሕሩ በላይ በሁለቱ ወንዞች መካከል ዛሬ ት/ቤቱ የተሰራበት ቦታ በባሕር ዛፍ፣ ግራር፣ ጥድ፣ አጋም፣ ቀጋና ኮሽም የተሸፈነ ነበረ። በኋላ ግን የሸክላ ሜዳ ከተቆፈረና ዛፍ ከተተከለበት በኋላ በምትኩ የከብት መዋያ ሆነ እንዲያውም በጣም የሚያሳዝነው አንዳንድ ግለሰቦች በተለይ



የሚኒስትሪ ፈተና የወደቁ ተማሪዎች በብስጭት ራሳቸውን ጫካው ውስጥ እየሰቀሉ ይሞቱ ነበር። ሌላው ደግሞ ሌባ የመነተፈውን ይዞ ከእዚህ ጫካ ውስጥ ከገባ ካለጥርጥር ያመልጥ ነበር። የታህሣስ ጦርነት ካለፈ በኋላ ከላይም ከታችም ሠፈሩ ስላደገ ሕዝቡም ቤተ ሰሪውም ስለጨመረ የአካባቢው ዕድሮች በመተባበር ይህንን ቦታ ለት/ቤት መስሪያ እንዲሰጣቸው ጠይቀው <<የእድር ት/ቤት>> በኋላም <<ሣህለ ሥላሴ ት/ቤት>> የተባለውን አቋቋሙ (ስለ ትምህርት ቤቱ አመሰራረት ዝርዝር ታሪክ የመጀመሪያው "ከቀበና ማህደር" መጽሄትን ከገጽ 25 እስከ 29 ይመልከቱ)። እኔም ሆንኩኝ አብሮ አደጎቼ ድንጋይ ከቀበና ጅረት እየሰበሰብን በመውሰድ ለት/ቤቱ መቋቋም የአቅማችንን አድርገናል። በተጨማሪም የዕድሮቹ ኮሚቴዎች ት/ቤቱ ከመሠራቱ በፊት ሲሰባሰቡ እንዳጋጣሚ ፀሐፊው ካልተገኘ እየጠየቁኝ የሚወያዩትን እጽፍ ነበር።

ከት/ቤቱም አልፈን የአቦን ወንዝ ሻገር ስንል ቤላ ይገኛል። ቤላ የሚለው "ቪላ ኃይለሥላሴ" ከሚለው የመጣ ይመስለኛል። አብዛኛው የቀበና ልጅ ፊደል የቆጠረው ቤላ መሄጃው ላይ ኗሪ ከነበሩት ከየኔታ ጥሩነህ ጋ ነበር። ደመወዛቸውን የሚከፍለው ትምህርት ሚኒስቴር ስለነበር እንደ ሌላው የቄስ ት/ቤት ወርሃዊ ክፍያ አያስከፍሉም ነበር። ሌላው የማይዘነጋው ደግሞ፤ ንጉሡ አልፎ አልፎ ወደ ቤላ እየመጡ በጦር ኃይሎች ሆስፒታል የሚገኙ ታማሚዎችን መጎብኘታቸው ነበር። ከቤላ ወረድ ብሎ ከጀርመን ኤምባሲ አጠገብ የቅንብቢት ሠፈር ይገኛል። ስለ ቅንቢቢት ከአንዳንድ ጓደኞቼ በስተቀር ብዙም የማውቀው የለም። አልፎ አልፎ ፋራንክ ሲኖረን ብረት ድልድይ አጠገብ ቃዲ ከሚባሉት ነጋዴ ሱቅ ቴምር ለመግዛት፣ እንዲሁም ወደ ቀ.ኃ.ሥ ት/ቤት መሄጃ ላይ ሻይና ፓስቴ መሸጫ ከነበረው ከአባ አብደላ ቤት በስተቀር ብዙ ዕውቀት አልነበረኝም።


## ማህበራዊ ህይወት

በቀበና አካባቢ ያደግነው ልጆች ዘመኑ ባመጣው የቧንቧ ውሃ ሳይሆን በውሃ ምንጭ ተጠቅመን ያደግን ነን። ሠፈርተኛው የቧንቧ መስመር ለማስገባት አቅሙ አይፈቅድም ነበር። ከላይ እንደተገለጸው ጃንሆይ ቤላ ሲመጡ ቀድመን ከደረቁ ድልድይ (ወንዝ የሌለበት የ13 ቁጥር አውቶቡስ የምትሄድበት) እንጠብቃቸው ነበር። ጃንሆይ ጉብኝታቸውን እንደጨረሱ ከቤላ እስከ ፈረንሳይ ለጋሲዮን በእግራቸው በጥቂት አጃቢዎች ተከበው የሚያልፉባቸው ጊዜያት ጥቂት አልነበሩም። የሚጓዙት በእግራቸው ስለነበረ በቀላሉ ይገኙ ነበር። ከአጠገባችን ሲደርሱ በአንድነት እጅ ስንነሳቸው ከሰላምታ ጋር አባታዊ መልስ ከመስጠታቸውም በላይ ለእያንዳንዳችን አንድ አንድ ብር ($1) ይሰጡን ነበር። በዚያን ጊዜ አንድ ብር ማለት ትልቅ ነበር፤ የገንዘቡ የመግዛት አቅም ጠንካራ ስለነበር። ሌሊቱን ሙሉ ቡሄ ጨፍረን የማናገኘውን በአንዲት ደቂቃ ያን ያህል ማግኘት ቀላል አልነበረም።

በአካባቢው ከተቋቋሙት የስፖርት ክለቦች ውስጥ የቀበና ናዳ አንዱ ነበር። ሌላው ደግሞ እኔና ጓደኞቼ ያቋቋምነው የኢትዮ-ፔይንት ነበር። እንዳጋጣሚ ሆኖ ለትምህርት ቤት የሻምፒዮን ውድድር በዋናነት ተፈሪ መኰንን ስላለፈ የመጨረሻው ውድድር ካምፖሎጆ (ስታዲዮም) ውስጥ ስለነበረ የገጠመንን ቡድን 4 ለ 1 በማሸነፍ የሻምፒዮኑን ደረጃ ስንወስድ እኔና ሌሎች ሶስት ልጆች ገና ሜዳውን ሳንለቅ ለቅዱስ ጊዮርጊስ አስፈርመውን ወደዚያ ስለገባሁ ለቀበና ናዳ ሳልጫወት ቀረሁ። ያም ሆኖ በእኛው ለተመሠረተው የኢትዮ-ፔይንት ግን እጫወት ነበር። ይህ እንግዲህ ወደ ሐረር መምህራን ማሰልጠኛ እስከምሔድበት ጊዜ ነበር። ቡድኑ ቀጣይነት ኖሮት ከሐረርም ስመለስ ታናናሾቼ ይጫወቱ ነበር።

በአጠቃላይ ተዘርዝሮ የማያልቀው የቀበና የቀድሞ ገጽታ በመጠኑ ይህን ይመስላል። በመጪው እትም ላይ ደግሞ "እነማን ነበሩ" በሚል ከመጀመሪያዎቹ የአካባቢው ሠፋሪዎች ስለተወሰኑት አጠናቅሬ ለማቅረብ እሞክራለሁ። ቸር እንሰንብት።

ጌታቸው በላይነህ (ዶ/ር)



የአሁኑ ቀበና፣ ኮሪያ ሰፈር አካባቢ ይህን ይመስላል

# የቀበና ወጋገን



አፈር ፈጭተን፤ አብረን አድገን
የቀበናን ውሀ ተራጭተን
የጃንሜዳን አፈር ጭረን
ሳንለያይ አንድ ሆነን
እህት ወንድም ተባብለን
በልጅነት በአብሮ አደግ ትዝታችን
ተንቀልቅሎ በውስጣችን
ያ የልጅነት ፍቅራችን
በጣም ሩቅ ብንሆንም ከቀያችን
ከተቀበረበት እትብታችን
አንድ አድርጎ አፈላልጎ አገናኘን
የሰፈር ልጅ የአብሮ ማደግ ፍቅራችን።
ደስ ያሰኛል ይበል ይበል
ለልጅ ልጆቻችን ገና ያልፋል
ቀበና ወጋገንሽ ታላቅ ድምፅሽ ያስተጋባል።

ከእጅግአየሁ በፈቃዱ



# ምንድነው ሚስጥሩ?

ምንድነው የቀቤነቱ፤ ነገሩ
ከውሀው ይሆን ሚስጥሩ?
የትዝታውና የናፍቆት ብዛቱ
አላስቀምጥ አለን በያለንበቱ።
ሙዚቃ ስንሰማ በሐሳብ መንጎዱ
ሰው እንዲህ ይሆናል አብሮ በማደጉ?
ከብይ ጨዋታው ነው ከጠጠር ውርወራው
ከቦሊ ቦሊው ነው፤ ከእግር ኳስ ጨዋታው
ከጢቢ ጢቢው ነው፤ ከሰኞ ማክሰኞው
የትኛው ነው እኛን
በፍቅር ገመዱ ሸብ አርጎ ያሰረው?
በጨዋታ መሀል ስንበሻሸቅ
ቅፅል ስም አውጥተን ባንዱ ስንስቅ
እንጫወት ነበር ሳንደባበቅ።
የዋናው ጉዳይስ የባዝሊን ቅባቱ
እንዳይነቃብን በወዝ መቅለጥለጡ።

ሁሉን በአንድነት እያከናወንን
ፓስቴ ቤትም ቢሆን አብረን እየሄድን
ሙሺ ቤትስ ቢሆን መቼ ተለያየን
በዛች በቀበና በልጅነታችን ምኑም አልቀረብን
ሽማግሌ አሮጊት እክብረን ያደግን
ሁሉ እናታችን ሁሉ አባታችን።
አሳድገውናል በጋራ ሆነው
የፍቅራችን ብርታት ለካስ ለዚህ ነው።
ቆይቶ ሆነና የገባኝ ነገሩ
ለካስ ሚስጥር አለው ከቀቤ መሆኑ።
የትም ብንወለድ ቀቤ ማደጋችን
ተሰደን ብንኖር በየማዕዘናችን
ቀበና አስተሳስሮን፤ ይኸው ተፋለግን።

ከግርማ ታደሰ



ጃምቦሪ

# አትቀስቅሱኝ!

አትቀስቅሱኝ እንድናገር
እኔስ ትቼው ሸፍኜው ነበር
ላለማንሳት ላለማስታወስ ነገር።
ዛሬ በቁርጡ ቀን ግን፤
ቤቴ ስገባ፤ ገና ከበር
መልዕክት አገኘሁ ከሩቅ ሃገር
በቀለማት ያማረ፤ ከቀበና ማህደር።
ኧረ ኡኡ! ኧረ እሪ!
አልኩ፤ ምላሽ ልሰጥ ለአብሮ አደግ ጥሪ።
አቤት ቀበና፤ አቤት ሾላው ሥር
የአብሮ አደጎችን ሹክሽክታ ፍቅር
የነበረና ያየ ይናገር።
ኧረ አትነካኩኝ ብዙ በሆዴ አለኝ
ኋላ አገርሽቶ እንዳይወጣብኝ
አቤት ቀበኖች
ይመስሉ ነበር የአንድ እናት ልጆች።
ድንበር ሳይወስነው ፍቅራቸው
ቦታ ሳያግደው መጠያየቃቸው
ያስቀናሉ አሁንም ቀርቦ ላወቃቸው።
የቀበና፤ የሾላው ሥር፤ ወይስ ዱቤ ባህር
የትኛውን ላስታውስ የትኛውን ላስቀር
ከልጅነት ዘመን ልጀምረው?
የሃገሬንማ፣ የእምዬንማ ሸፍን ልብስ ላድርገው
የእናት ጓዳ የእናት ነው አደባባይ አላሰጣው።
ነፃነት ጠፍቶ የድብብቆሽ ሲሆን ሕይወት
ኑሮ ሲከብደን በቃኝ ሃገሬ፣ በቃኝ ሰፈሬ
ብለን የወጣንበት
በስደት ሃገር የሃገሬ ወንዝ ይብላኝ፤
ብለን ባልንበት
እኔና ሮዚ ናፍቆታችንን ጀምረን ያልጨረስንበት።
ኧረ አትቀስቅሱኝ
ኋላ አገርሽቶ እንዳይወጣብኝ
ኧረ ስንቱ፤ ያም ታለፈና ሆኖ ነጻነት
መፍራት መደበቅ፤ ሲያበቃ ጭንቀት
በሰላም መውጣት፤ መግባት ሲጀመር
እዚህ በስደቱ አገር፤
አድማ ተመታ፤ ጎራ ተመታ
ጎሳ ነገሠ በአገር ልጅ ቦታ።
ቀበና አደጎች ግን
ከቤተሰባቸው የወረሱትን



አይናለም ተስፋዬ እና ሮዛ ደስታ፤ የሮዛ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት በተፈጸመበት ዕለት (1996) መለያየት ጭንቅ ሆኖባቸው።

አብረው በልተው፤ አብረው ጠጥተው
አብረው ተክዘው፤ አብረው አልቅሰው
አብረው ደግሰው፤ አብረው ሠርገው
በፍቅር ኖሩ፤ በእውነቱ ሆነው።
የተነገረን ከቤተሰባችን
ስማችን እንጂ ዘር አልነበረም
በትምህርት ቤት ሆነ፤ በሰፈር የለም።
ከየት ቦታ ከማን ተወለድን
ቦታ የለውም ቀበና ላደግን
መኖር ባህል ነው፤ ከበን ተካበን።
ኧረ አትቀስቅሱኝ
ኋላ አገርሽቶ እንዳይወጣብኝ

በፍቅር እንዳደግን በፍቅር እንደኖርን
ጌታ በመንግሥትህ ሁላችን አስበን።

ቀበኖች እወዳችኋለሁ።
አይናለም ተስፋዬ (ብጥቃ)

እንዴው ምናለ ያ ሾላ ዛፍ
በእቅፉ ያሳደጋት የሮዝ አበባ ስትረግፍ?
(ወርቁ ዳመና፣ እሑድ 24 ማርች 2013፤
ፍራንክፈርት አየር ማረፊያ፣ የሮዛን ዜና ዕረፍት እንደሰማሁ)



# ሾላው

የሰፈር አድባር ቆሌው
የግንቦት ልደታ ሙሽራው።
ሾላው
የጣፋጭ ፍሬ መጋቢው
ከዝናብ ጸሀይ መጠለያው
ሾላው
እርጅና ተጭኖህ ነው
እርግፍ እርግፍ የማትለው ?
እንደድሮው።
ሾላው
እባክህ ታሪክ አውጋኝ
የድሮ ዛሬ፤ ልዩነትን አስረዳኝ ።
ድሮ ድሮ ሳውቅህ
ንፍሮ ቂጣው ሲቀርብልህ
ቅቤ ዘይት ሲቀባቡህ
ጠላ ቡና ሲደፋብህ
ያ ሁሉ የግብር መዓት
ሲከፈልህ ከዓመት ዓመት
ስትጫጫስ፤ በአምልኮ በምትሃት
ግርም ይለኝ ነበር
ዛፍነትህን እጠራጠር ።
አንተ አረንጓዴ ፍጡር
ቀውላላ ነገር
የአድባሮች ሁሉ አድባር።

ኖረ አልኖረ የቤት ቁጥር
ሾላው ጋ ነው የኛ ሰፈር
ማለት የተለመደ ነበር።
ዛሬ ቆሌ ቢስ ትመስላለህ፤ ቆሌው
መክሳት መገርጣትህ ምነው?
ትናፍቃለህ እንዴ
እኒያን የድሮዎቹን
ያለፉትን፤ የተበተኑትን?
እነማን ትዝ ይሉሃል
የትኞቹን ታዝበሃል
በክንዶችህ ላይ የዘለሉትን
በጥላህ ስር የተደበቁትን
ወይስ
ወገብህን ተደግፈው
ፍቅር በፍቅር የሆኑትን
ወይስ
በጨለማ፤ በስካር ካንተ ጋር የተጋጩትን
አዬ ሾላው ! የድሮ አድባር
ዋና ምልክት የሰፈር
ኑርልን እባክህ
ቢቀርብህም የዓመት ግብር።

ከደገኛው
(ግንቦት 26 ቀን 2007 ዓ ም)

# ያኔ ትንሽ ሳለን

ያኔ ትንሽ ሳለን
ቆርኪ፤ ብይ አጋጭተን
የሸቦ መኪና ፤ ኩሽኔታ ነድተን
በአንድ ላይ ቦርቀን
ፍጹም ተደስተን።
ደግሞ እንጣላለን ፤ እንዋገራለን
ወዲያው ተሳስቀን
ብስኩት፤ ፓስቴ ገምጠን
ሰላም ይሆንና፤ እንታረቃለን።
የእኛ ታላላቆች
የጃንሜዳ አንበሶች
የኳስ ቡድን ፈጥረው
ሌላ ሰፈር ሄደው
ሲመጡ ድል አርገው፤
ከኬላ ከሼላ
ሽልማት አላቸው
ብዙ ጣሳ ጠላ።

ከደገኛው
(ግንቦት 3 ቀን 2007)






# ጃምቡሌ፤ ቡሌ

ጃምቡሌ፤ ቡሌ
አረሩ ገድሌ
ከኮንሶ ነህ ከነገሌ?
ጃምቡሌ፤ አንተ የጥዋት ደወል
ከእንቅልፍ አንቂ፤ አላርም ነገር
የሞት፤ የቀብር ትዊተር
ጃምቡሌ፤ መቼም የአንተ ሥራ
ቀን ቀን ስለ ሙታን አቦ ጋሪ
ማታ ማታ ግን ዳንኪራ።
    ጃምቡሌ
    የመንገዱ ቲያትረኛ
    ዋናው ተጠሪ ለዕድር ዳኛ።

ያ የማታ ማታ ቋንቋህ
በሳቅ የታጀበ ለቅሶህ
ትርጉሙን ሳትነግረኝ ጃምቡሌ
ድሮ ድሮ ምን እንዳደረጉህ ደጃች ገድሌ።
    ህይወት ላንተ ምን ነበር ?
    ሞትን ሁሌ በጥሩንባ ስታከብር።
ውለታ ቢስ ነው ሞት
የአንተን የወዳጁን ነፍስ እንኳን አልማራት
አገልጋዩን አንተን ወስዶ፤
    ቀበናን ፀጥ፤ እረጭ አደረጋት።

ከደገኛው (ግንቦት 1 ቀን 2007)



ማን ይደፍረናል!

# ጃንሜዳ

ሳድግም ሆኜ ጎረቤትህ
በመወለዴ በአካባቢህ
ስዘልብህ ስሮጥብህ
ስወድቅና ስነሳብህ
ስንከባለል በያቅጣጫህ
ደክሞኝ ላቁም እንጅ እኔ
አንተ ምን ገደብ አለህ።
  ከጫፍ ለጫፍ ለመመልከት
  ዐይንን የምታታክት
  ያለጠባቂ ተለቅቄ
  ያደኩብህ ቦርቄ
  አንተ ጃንሜዳ የእኔ ብርቄ
  ግልጋሎትህን ሳስታውስ አሁን እንዲህ ርቄ
  ከቶ መግቻ አጣሁለት ስለአንተ አውርቼ ማድነቄ።
ስፍር ቁጥር የሌለው የሰጠኸው አገልግሎት
ሙዚቃ መለማመጃ ወታደር ማሰልጠኛነት
ሙዚቀኛው በየረድፉ
መሳሪያውን አርጎ ባፉ
ከበሮአቸውን ሲነርቱ ጡሩንባቸውን ሲነፉ
ይረግጡህ ነበር ሳይከፉ
እስሚዋሀድ ድረስ ጣዕመ ዜማና ሰልፉ።
  ያ አዲስ ወታደርም
  ከያቅጣጫው ተመልማዩም
  ቀኝ እጁ ከግራው እግር
  መሄዱን አውቆ እስኪማር
  ጠዋት ከማታ ሳይቀር
  ግራ ቀኝ ይልብህ ነበር።
የእኔ ብጤውም ወጣቱ
ባልተበላ ጉልበቱ
ወፍ ተንጫጭቶ  ከመንጋቱ
ጤዛ ሳይለቅ በጠዋቱ
ይሯሯጥብህ ነበር እስኪጠልቅ ጀንበር በመምሸቱ
ማየት እስከሚሳነው ወጼት እንዳለች ኳሲቱ።
  በሩጫ በልጠው የከነፉ
  በዓለም አድናቆት ያተረፉ
  እነ አቤም ሆነ ማሞ፣ ብሎም ሌሎች ያለፉ
  በአንተ ላይ ነበር ልምምዱ
  ገና ሀ ሲሉ አሀዱ
የገናም በዓል ሲደርስ
ተመልካች አምሮ በሀገር ልብስ
ተጫዋች ሩር ሲያተራምስ
ቆልመም ባለው ቆመጡ በከረመው ሲጠጣ ጭስ
በአንተ ላይ ነበር ወግ ድግስ
በሆንከው የሜዶች ንጉስ።
  ለጥምቀት ታቦት ተሰብስቦ
  በምእመናን ታጅቦ
  ዳሱ ተጥሎ በየቦታው
  ሲነገድብህ የሚውለው
  ሻይ ዳቦ ሆነ ሻማው
  በቀስተ ዳመና ቀለምታው
  ባሸበረቀ ዱላው
  ታጅቦ ጭፈራው የሚደራው
  የሚዋኝብህ ዋናው
  ዜጎች በነገር ተፈላልገው
  ሲፈናከቱ የሚታየው
  ታቦት መልሶ እስኪያገባ
  ነበር ባንተ ላይ ስብሰባ።
የቀይ መስቀሉ ድግሱ
የውጭው ዜጋ ትርምሱ
ፖሎ ጨዋታው በፈረሱ
ክቡር ዘበኛው ባልደራሱ
በእድገት በህብረት ዘመቻ
ሰልፍ ግራ ቀኝ መምቻ
ለመጨረሻ እስክረግጥህ በዛ በትርምሱ
ምስክር እሆንሃለሁ ለአገልግሎትህ ለጨዋታ ድግሱ
ታሪክ እንዲያስታውስህ አንተን የሜዶች ንጉሱ።

ሰለሞን (ጋንፉር)



# የፎቶ አምድ



ከአምናው የመሰባሰቢያ ቀን ታዳሚዎች በከፊል (2014)



“ከቀበና ማህደር” ሲመረቅ (ጁላይ 5 ቀን 2014)







ያምናው የቤተሰብ ቀን ድግስ



ከትውልድ ወደ ትውልድ



“የቀበናን ግሪን ካርድ በማግኘታችን ደስተኞች ነን”



ሰላም ነው?!



የድግሱ እመቤቶች



“የመጽሔቱ የመጀመሪያ እትም ኮፒ ደርሶናል”




(ፎቶ፤ ገዛኸኝ ታደሰ)




የፎቶ ክፍለ ጊዜ



"ለሚቀጥለው በሰላም ያድርሰን" አስተባባሪዎቹ



ቃኘው በኮሪያ የስፖርት ክለብ




CHICAG
SURF
CHAMP